# ኢትዮጵያ - ብሔራዊ የአገር ማዳን ጥሪ

ኢትዮጵያን የማዳን መድረክ

SAVE ETHIOPIA FORUM

ታህሣሥ ፳፻፲፮ ዓም/ December 2023

Email - SaveEthiopiaForum@gmail.com

# ኢትዮጵያን የማዳን መድረክ - ማንነት

የዚህ ሰነድ አዘጋጆች በየአህጉራቱ የምንኖር ግለሰቦች ነን። ለረጅም ጊዜ በኢትዮጵያና በውጭ አገራት የሥራ ልምድ ያካበትን፣ በትምህርት ደረጃም በየእርከኑ በቂ የሆነ እውቀትና ሥልጠና ያለን ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነን። እምነታችንም በመልካም አስተዳደር፣ በኢትዮጵያ አንድነት፣ በእኩልነት፣ በዴሞክራሲ፣ በስብዊ መብቶች መከበር፣ በሕግ የበላይነት፣ በግልፅነት፣ በተጠያቂነት አሰራርና በህዝብ ልዕልና ላይ የተመሠረተ ነው።

# ኢትዮጵያ - የአገር አድን ጥሪ
## ክፍል 1

ማውጫ


አጠቃላይ አጭር ማብራርያ ....................................................................1
የ63 ዓመታት የፖለቲካ ጉዞ - ከ1953 – 2016 ዓም..........................................2
የብልጽግና ዘመንና በአማራው ላይ የዘነበው ጥቃት..........................................3
በኢትዮጵያ ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችና ያመለጡ ዕድሎች......................................6
አካታች ሥርዓት ለመገንባት ዕድሎች ለምን ሊያመልጡ ቻሉ? ...................................11
ዛሬ፣ በብልጽግና ዘመነ መንግስት ያለው ሁኔታ...............................................13
በሀገሪቱ የታጠቁ ኃይሎች.....................................................................14
ሊሆን ከቻለ 1 (Scenario 1) - በመከላከያውና በፋኖ መሀከል የሚደረገው ጦርነት ከቀጠለ..........15
ሊሆን ከቻለ 2 (Scenario 2) - ብሄረተኛ ኃይሎች በማበር ፋኖን አዳክመው የበላይነት ከተቀዳጁ.........16
ሊሆን ከቻለ 3 (Scenario 3) - ብልጽግና ከ40 ሚሊዮን የአማራ ህዝብ ጋር ጦርነት ከቀጠለ..........17
ሊሆን ከቻለ 4 - (Scenario 4) ጦርነቱ በአማራው/በፋኖ እና በመከላከያው መሆኑ ቀርቶ አድማሱ ከሰፋ..........18
ሊሆን ከቻለ 5 - (Scenario 5) - ፋኖ ሰፊ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ስራ ካከናወነ..........19
ሊሆን ከቻለ 6 - (Scenario 6) - ሁለቱም ወገኖች ጥሪውን ከተቀበሉ ..........19


## ኢትዮጵያ - የአገር አድን ፍኖተ ካርታ - ክፍል 2


የ63 ዓመታት አገዛዝ ያስከተለው መዘዝ፣..........21
ዓላማና ግብ፣ ..........22
የሽግግር መንግስት ለምን ያስፈልጋል?..........22
የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ምስረታ ፣ ..........24
ወቅት 1- የቅድሚያ ወቅት ተግባራት..........24
ወቅት 2 - የመካከለኛ ጊዜ ተግባራት..........26
ወቅት 3 - የሩቅ ጊዜ ዕቅዶች ..........27
መደምደሚያ..........28

# ኢትዮጵያ - የአገር አድን ጥሪ

## አጠቃላይ አጭር ማብራርያ

ይህ ሰነድ የኢትዮጵያ አስከፊና ህልውናዋንም የሚፈታተን መስቀለኛ መንገድ ላይ መቆሟን ይገልፃል። ይህም ሁኔታ የሚያሳየው እንደ ሉዓላዊ አገር የመቀጠል፣ ወይም በቅርቡ እንዳየናቸው አገሮች የመፈራረስ፣ ለአካባቢው አገሮችና ለሰፊው ቀጠና የቀውስ ምንጭ መሆን ነው። ያ እንዳይሆን ውድ ዜጎችዋ በረዥም የታሪክ ሂደት ያካበቱትን እሴቶችና የአብሮነት መንፈስን ይዘው መቀጠል ይጠበቅባቸዋል።

ባለፉት 60 ዓመታት ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለዕድገት የተደረጉት ህዝባዊ ትግሎች በጥቂት አምባገነኖች ተነጥቀዋል። እነኝህም አምባገነኖች ሁሉም የሚጋሩት ጠባያቸው ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ህዝቡን ያካተተ መንግሥት አለማቋቋማቸው፣ በጠመንጃ መተማመናቸውና የመንግሥትን ሀብት ለራሳቸው እያዋሉ የለየላቸው አምባገነኖች መሆናቸው ነው። ይህ ሰነድ ያሳለፍናቸውንና የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን እያስጨበጠ ከታሪክ አለመማር የሚያድርሰውን አገራዊ አደጋ ያሳየናል። በዚህ ሰነድ በ1953 ዓ ም አፄ ኃይለ ሥላሴን ከስልጣን ለማውረድ በተደረገው ሙከራ የተጀመረው ሂደት፣ ከዚያ በኋላ በየዘመኑ የተፈጠሩ ዕድሎች፣ በ2011 ዓ ም የተፈጠረውን ጨምሮ፣ እንዴት እንደመከኑና ሀገሪቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለአስከፊ ሁኔታ እንደዳረጉና ሕዝቡን ለከፍተኛ መከራ እየማገዱ እንደሄዱ ከእነማስረጃው ቀርቧል ።

በቅርብ ከሥልጣን የተወገደው በህዋህት የሚመራው የኢህአደግ አንድና በኦሮሙማ የሚመራው የኢህአድግ ሁለት ብልፅግና ካለፉት መንግሥታት የተለዩ ናቸው። የሚያምሳስላቸው እንደአለፉት መንግሥታት ሁሉ አቃፊ መንግሥት ያልመሠረቱ፣ በጉልበት የሚመኩና በተለይ የአገሪቱን ኃብት እንዳሻቸው ለግል ጥቅም ያዋሉ መሆናቸው ነው። ከበፊቶቹ የሚለዩበት ግን ኢትዮጵያን ለዘመናት የሚከፋፍል የዘውግ ሥርዓት መሥርተው በሥራም ላይ ማዋላቸው ነው። ይህም ከዓለም አገሮች ሁሉ የተለየና ኢትዮጵያን ወደ መበታተንና ሕዝቧን እርስ በርስ ወደሚያፋጅ ጎዳና የሚወስድ ነው።

አሁን በብልፅግና መንግሥት ስር ያለችው ኢተዮጵያ ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ ቀውስ ባሻገር ወደ ዘመነ መሣፍንት ጊዜ የሚወስደን ከአገር መከላከያው ሌላ 8 ግዙፍና አነስተኛ የሆኑ ወታደራዊ ኃይሎች በአገሪቱ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። እነኝህ የታጠቁ ኃይሎች ጦራቸው ቢደመር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሲሆን ዘመናዊ ትጥቅ ያላቸው ናቸው። በአንድ ላይ ቢቆሙ የአገር መከላከያው ሊቋቋመው አይችልም። አሁንም በተናጠል እየተፈታተኑት ነው። በብልጽግና ውስጥ ያሉትም ባለተረኛ ነን እያሉ አገሪቷን እየተፈታተንዋት ነው። የህዝብም ትግልና ድምፅ እየታፈነ ነው። ወዴት እያመራን ነው? የሚለው ዋና ጥያቄ ሆኗል።

እነኚህን የታጠቁ ኃይሎች በተናጠልም ሆነ ወይም አንደኛው ከሌላው ጋር እየወገነ የአገሪቷን ህልውና እንደሚፈታተኑ በግልፅ ተቀምጧል። አሁን እንደሚታወቀው ፋኖ ስሙም እየገነነ ተግባሩም በጦር ሜዳ እየተመሠከረለት ሄዷል። የኃይል አሰላለፉን በ" ሊሆን ከቻለ" (scenario) በማለት ሁኔታዎች በስዕላዊ ገለፃ ኢትዮጵያን ወዴት ሊወስዱ እንደሚችሉ የሚያመላክቱ 6 ቢሆንታዎችን (scenarios) ከእነ ማስረጃዎቻቸው ተሰንደዋል። ለምሳሌ በመከላከያና በፋኖ መሐል ጦርነቱ ከቀጠለ ምን ሊሆን እንደሚችል፣ እንዲሁም ፋኖ ሌላውን የማህበረሰብ ኃይሎች ከጎኑ ካሰለፈና የሰከነ የዲፕሎማሲ ሥራ ከአካሄደ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚሉት ይገኙበታል።

በመጨረሻም ኢትዮጵያን ካሁኑ ችግሯ አላቆ መፍትሔ የሚሆኑትን ሀሳቦች በፍኖተ ካርታ መልክ ተገልጿል። ይህም ያለፈውን የተጠቀሱትን የሩቅና የቅርብ ታሪክ (ለምሳሌ አካታች መንግሥት አለመኖሩ አስቦ አሁን ደግሞ አገሪቱ የወደቁ አገሮች (failed states) ከሚባሉት ተርታ አውጥቶ፣ ኢትዮጵያን ከገባችበት ማጥ ለማውጣት ከ6ቱ "ሊሆን ከቻለ" (scenarios) ውስጥ አንድ ምርጫ ብቻ እንዳላት ያመለክታል። አምስቱ ጎዳናዎች ኢትዮጵያን ወደ ሲዖል የሚወስዱ ሲሆኑ፣ አንዱ ብቻ የድህንነቷ ጎዳና መሆኑን ያሳያል።

ስለዚህ ይህ ሰነድ ኢትዮጵያን የሚሉ ሁሉ የደህንነቷን ጎዳና ለመከተል አቅጣጫውን የሚያመላክት ፍኖተ ካርታም አካቷል። ይመልከቱት፣ ያንቡት፣ ያሰላስሉት፣ ያዳብሩት፣ ኢትዮጵያን ለመታደግ የበኩልዎን አስተዋጽኦ ያበርክቱ። ኢትዮጵያን ለማዳን ሁሉን አካታች የሆነ ወደ ሽግግር መንግሥት ምሥረታ የሚያድርስ መንገድ ፍኖተ ካርታው ቀይሷል። የሽግግር መንግሥት ለምን እና መቼ፤ እንዲሁም የሽግግር መንግሥትን ይዘት ይጠቁማል።

ይህም ሰነድ ኢትዮጵያን ለማዳን የተዘጋጀ ስለሆነ የሁሉን መተባበር፣ መደማመጥና መከባበርን ይጠይቃል። ዋናው ትኩረታችን አገርን ከውድቀት፣ ከእርስ በርስ እልቂት ማዳን መሆን አለበት።

# ኢትዮጵያ - የአገር አድን ጥሪ

# ክፍል 1

## የ63 ዓመቶች የፖለቲካ ጉዞ - ከ1953-2016 ዓም

*መግቢያ*

ኢትዮጵያ አያሌ ፈተናዎች ከፊቷ ተጋርጠውባታል። ገሚሶቹ ከታሪክ ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ፣ የተቀሩት ደግሞ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች መፍትሄ ሽተው ያላገኙላቸው፣ የተኮላሹ፣ በእንጥልጥልና በጅምር የቀሩ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ በልጆቿ መሀል የልዩነት ምክንያት ሆነው እያናቆሩ የሚገኙ ናቸው።

ኢትዮጵያ እንደ ሰው ብትናገር፣ "መከራችሁ በዝቷል፣ መቋቋም ያቃታችሁ ትመስላላችሁ፣ ስምምነትም አጥታችኋል። በረባ ባልረባው ትናቆራላችሁ። ትዳማላችሁ፣ ትፋጃላችሁ። ሲቃውና ጩኸቱ እንዲሁም እንደጎርፍ የሚፈሰው ደም ህሊናዬን ሰርስሮ እየገባ ሰላም ነሳኝ፣ ደከመኝ፣ ጉልበቴ ዛለ" እያለች ምርር ብላ ትወቅሰን፣ ትታዝንብንም ነበር። ስለዚህም ብሶቷንና ዋይታዋን፣ ሃዘኗንም ሆነ የለቅሶ ምክንያቶቿን ከስረ-መሰረቱ ለመረዳት ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን በጥቂቱ እንቃኛለን።  ከቅርብ ታሪካችን በመነሳት ያካበትነው ትምህርት ስላለ ስህተቶቻችንን እንዳንደጋግም ከታሪካችን ልንማር ይገባል።

በመጀመሪያ ግን፣ በ2011 ዓም የስልጣን እርካብ ላይ የተፈናጠጠው የጠቅላይ ሚንስትር ዓብይ መንግስት፣ ፍትህን፣ እኩልነትን፣ ሰላምንና የኑሮና የኢኮኖሚ መረጋጋትን ሊያመጣ ባለመቻሉ፣ በህወሓት የበላይነት በሚመራው ኢህአዴግ ዘመን፣ ማለትም ከ1983 ዓም ጀምሮ በነበረው ጊዜ ስር መስደድ የጀመሩት ችግሮች እየተባባሱ ሄዱ።

የኢኮኖሚ ችግሩ እጅጉን በረታ። በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎችም ረሀብ ገባ። የመሠረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ ንረት ከአብዛኛው ዜጋ የመሸመት አቅም በላይ ሆነ። በ2013 ዓም በተካሄደው ጦርነት ምክንያትም ሆነ የኦሮሞ ብሔርተኛ ኃይሎች በሚያካሂዱት ወታደራዊ ጥቃት ሰበብ ከ4 ሚልዮን በላይ የሚገመቱ ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያዎች ይገኛሉ። የሀገሪቱ ገንዘብ የመግዛት አቅም ከመዳከሙ ባሻገር፣ ባንክ ቤቶች ለስራ እንኳን የሚረዳቸው በቂ ገንዘብ የላቸውም። ስራ አጥነቱ እየተበራከተ ሄዷል። የታጠቁ ቡድኖች በፈለጋቸው ሰዓትና ሁኔታ ጥቃት ሲሰነዝሩ የሚመክትም ሆነ ጉዳዩን ተከታትሎ ለዜጎች ጥበቃ የሚያደርግምና ሌላ መፍትሄ የሚሰጥ መንግስታዊ ኃይል የለም። በእነዚህም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች፣ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በጠራራ ፀሀይ ዜጎችን አግቶ ከህዝቡ አቅም በላይ የሆነ የገንዘብ ክፍያን መጠየቅ የቀን ተቀን ድርጊት ሆኗል። በርካታ የታገቱ ዜጎችም ለሞት ተዳርገዋል። የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሬ እየጠፋ መሄዱ ንግዱን አቀዛቅዟል። የስራ አጡ ብዛትም ጨመሯል። ሕዝቡም ለከፋ ድህነትና ለተባባሰ ሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተዳርጓል። በአጠቃላይ፣ ከህዝቡ አቅም በላይ የሆነው የኢኮኖሚ ችግሩና እንድምታው፤ ስርዐቱን ለማፍረስ ቀን እየቆጠረ ያለ ፈንጂ ነው።

በሀገሪቱ ውስጥ የነበሩት የታጠቁ ሀይሎች አደረጃጀት፣ ስብጥርና ቁመና በዘረኝነት አስተሳሰብና ዕምነት ላይ የተመሠረተ ስለነበር፣ በ2010 (2018) በጥገናዊ ለውጥ የመጣው የፌደራላዊ መንግስት ሌሎችን የክልል ሃይሎችን ለመቆጣጠር ያለው አቅም ብቃትና ተነሳሽነት ደካማ ነበር። ይህ ሁኔታ ሀገራችንን ከ2013 ዓም ጀምሮ ለሁለት አመታት በፌደራል መንግስቱና በህወሃት መሀከል ለተካሄደው አውዳሚ ጦርነት ዳርጓታል። ያ በወንድማማቾች መሐል የተካሄደ ረጅምና አውዳሚ ጦርነት ሀገሪቱን እጅጉን ደቆሳት። ዜጎች እንደቅጠል ረገፉ፣ አካል-ጉዳተኞች ሆኑ፣ ተፈናቀሉ፣ ደኸዩ። ሴቶች ኢሰብዓዊ በሆነ ደረጃ ተደፈሩ። በርካታ ዜጎች ለከፍተኛ ውርደትና ጉዳት ተዳረጉ፣ ከመኖሪያቸው ተፈናቀሉ፣ በየማጎሪያዎች ተወርውረው እርዳታ የሚጠባበቁ ተረጅዎችም ሆኑ። የተለያዩ ተቋማት፣ ፋብሪካዎች፣ ሀኪም ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወ. ዘ.ተ. ይሁን ተብሎ በተፈጸመ ጥቃት ፈራረሱ። ትምህርት ማስተማር ተቋረጠ። ሀገርና ዜጎች ላይ የደረሰው ስብራትና ቁስል ባለመሻሩ፣ ኢትዮጵያ በታሪኳ ገጥሟት የማታውቀው ዓይነት ፈተና ውስጥ ወደቀች።

የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት፣ የጉራጌ ማህበረሰብ፣ የጉጂ፣ የቦረና፣ የጋምቤላ፣ የአፋር፣ የሱማሌ ክልልና የሌሎች ማህበረሰብ አካላት ፈታኝ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ይገኛሉ። የዘር ፖለቲካው የፈጠረው ጽንፈኛነትና ሀገሪቱ የገባችበት የእርስ በርስ ፍጅትም ችግሩን አወሳስቧል። ዜጎችን ለበለጠ መከራ ዳርጓል።

በጠቅላይ ሚኒስቴር ዓብይ ዘመን፣ በጸጥታ መናጋትና በእርሻ ግብዓቶች እጦት ምክንያት የእርሻ ጊዜ ተስተጓጎለ። ይህ ሁኔታም በመጪው አመት ከፍተኛ የምርት እጥረት ያስከትላል ተብሎ ይገመታል። እያሻቀበ ከሚሄደው የኑሮ ውድነትና ከእህል አቅርቦት ማሽቆልቆል ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ ከፍተኛ ችግር እንደሚገጥማት፣ ብሎም ርሀብና ችጋር ጥቂት አካባቢዎችን ብቻ ሳይሆን መላ ሀገሪቱን ሊያዳርሱ እንደሚችል ይገመታል። በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር ህዝብም ለከፍተኛ ረሀብና ዕልቂትም ይዳረጋል ተብሎ ይታመናል።

ኢትዮጵያን የመከራ አዘቅት ውስጥ እንድትዘፈቅ የገፋፉ በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ በመንግስትና በተለያዩ ቦታዎች በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ኃይሎች መሀል የሚካሄደው ጦርነት እየተንቦገቦገ መቀጠሉ ሙሉ ህዝቧን ሠላም ነስቶ፣ ሀገሪቷንም ለቀጣይ ውድመት ዳርጓታል። ቆም ብለን ካላሰብንና ለጎሲናችን ካልታዘዝን፣ በምን መልክ ሊቋጭ እንደሚችል መተንበይ አስቸጋሪ ሆኖብን በአፍጢማችን እስከምንደፋ የቁልቁለት ጉዟችንን እንቀጥላለን ማለት ነው። ሀገሪቱ መድማቷን ትቀጥላለች፣ ወገን ያልቃል፣ ኢኮኖሚው ይበልጥ ይዳሽቃል። ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ አልፎ ቀጠናውን በሞላ የሚያናጋና የቀይ ባህር አገሮችን ብሄራዊ ደህንነት አጣያያቂ ያደርጋል። ስለዚህም፣ አሁን የጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ መንግስት የሚያራምደው የተዛባ ትርክት ከኢትዮጵያ፣ ከአፍሪካም አልፎ ለዓለም አስጊ ሁኔታዎችን በመፍጠር ይቀጥላል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ሀገራችን ከሰሜኑ አውዳሚ ጦርነት ጉዳቶች ገና ሳታገግም፣ መንግሥት የአማራ ክልል ልዩ ኃይልን ለማፍረስና ፋኖንም ትጥቅ ለማስፈታት በመነሳቱ፣ ያውም ሥርዓቱ በመንገዳገድ ላይ በሚገኝበት ወቅት፣ በፌደራል መንግስቱና በፋኖ መሀከል ጦርነት ተቀሰቀሰ። ይህ ጦርነት መጠነ ሰፊና የኢትዮጵያን መፃኢ እድል የመወሰን አቅሙ ጎላ ያለ በመሆኑ፣ የሁሉም ሀገር-ወዳድ ዜጋዎችን ትኩረት ይሻል። እናም፣ ለጉዳዩ መነሻ የሆነውን የፀረ-አማራና የፀረ-ኦርቶዶክስ ክርስትያን ትርክት እንዴት እንደተጀመረ መጠነኛ ዳሰሳ ማድረግ ተገቢ ነው።

ከ50 አመት በፊት ህወሃትን ለማቋቋም ገና ውጥኑ ሲነደፍ ሥርዓትን በመለወጥ ትግል ላይ ያተኮረ ሳይሆን አማራው ዒላማ ተደረገ። ፀረ-አማራ ትርክት ተቀነቀነ። እንደ ህወሃት ሁሉ በትግራይ በረሃ ለትግል የተሰለፉ እንደ ኢህአፓ እና ኢዲዩ የመሳሰሉ ሕብረ ብሄራዊ ድርጅቶች፣ በውጊያ ጭምር ከትግራይ እንዲወጡ ተደረገ። ከዚያም፣ ህወሃት ዋነኛ ዒላማ ያደረገው አማራው ላይ ሙሉ ትኩረቱን አሳረፈ። በ1983 ዓም ህወሃት ስልጣን እንደያዘም፣ የፀረ-አማራው ትርክት መንግሥታዊ አቅም በማግኘት ጎለበተ። ዘመቻው ቀጥሎ፣ በአንድ ወቅት፣ የህወሃት አመራር አባላት "አማራንና የተዋህዶ ክርስትና ሃይማኖትን ዳግመኛ ሊነሱ እንደማይችሉ አድርገን ቀብረናቸዋል" አሉ።

**የብልጽግና ዘመንና በአማራው ላይ የዘነበው ጥቃት**

በህወሃት ይመራ የነበረው ኢህአዴግ 1 ተወግዶ በኦህዴድ የሚመራው ኢህአዴግ 2 (ብልጽግና) ተተካ። ኢትዮጵያ የገጠሟት ሀገራዊ ችግሮች ሊወገዱ ይችላሉ የሚል ታላቅ ተስፋ ቢፈነጠቅም፣ ሳይውል ሳያድር ህልሙ ወደ ቅዠትነት ተቀይሮ ችግሩ ተባባሰ። ሁለቱም የየራሳቸውን ብሔር የበላይነትና ያለፈውን ታሪክ ሽረው የየራሳቸውን አዲስ ታሪክ በመፃፍ አባዜ ላይ ተጠመዱ። በአማራውና በኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ላይ ያነጣጠረው ትርክትም ቀጥሎና ተባብሶ ብዙ በደል ተፈጸመ።

በደል አመጽን ይወልዳል እንዲሉ፣ ከ30 አመታት በላይ የተካሄደው የህወሃት/ኢህአዴግ የግፍ አገዛዝ ሌላ ግዙፍ የተቃዋሚ ኃይልን ወለደ። ሳይበድል በድሏል፣ ሳይጨቁን ጨቁኗል፣ ሳይዘርፍ ዘርፏል በማለት በሰላም ይኖር የነበረውን የአማራውን ህዝብ፣ ነጋዴ ከአርሶ አደር፣ ወንድ ከሴት፣ ትልቅ ከትንሽ፣ ምሁር ከተማሪ ሳይል ዳር እስከዳር አነሳሳ። ትናንት በአድዋና በማይጨው

ለኢትዮጵያ ህልውና ህይወቱን ጭምር የገበረውን የአማራ ህዝብ ዛሬ ለራሱ ህልውና እንዲታገል ተደረገ። ከኢትዮጵያዊነቱ ውጭ የተለየ ሌላ ማንነት ያልነበረው ይህ የህብረተሰብ ክፍል፣ መጀመሪያ የመቀመጫዬን እንዳለችው እንስሳ ለህልውናው እንዲቆም አስገደዱት።

ታላቅ ሀገራዊ ስብዕና ተላብሶ ይኖር ከነበረበት ማማ አውርደው መሬት በመፈጥፈጥ፣ እንደእነሱ ጠባብና ጎጠኛ ዓላማቸውን እንዲጋራ ለማድረግ እየጣሩ ናቸው። ለአንድነት፣ ለህብረት፣ ለኢትዮጵያዊነት ሲሟገት የነበረው አማራ፣ በጠባብ ማንነት ላይ ብቻ የተሸበበ ጥብቆ እንዲያጠልቅ የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል፣ እያደረጉም ናቸው። ይህ ውጥን መሳካት/አለመሳካቱን ታሪክ ይፍረድ ብሎ በመተው፣

ለዘመናት የተገነባው የአማራውም ሆነ የሌሎች የኢትዮጵያ ዜጎች ማንነት በቀላሉ ሊናድ እንደማይችል በአጽንኦት መናገር ይቻላል። በተጨማሪ፣ ሁሉን አቃፊ የሆኑትና በኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሰረቱት የተዛምዶና የትሥስር ብሂሎች፣ እንዲሁም የሚጋሯቸው ሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች (እስልምናና ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ክርስትና) ሀገራዊ ማንነታቸውን ተላብሰው ይዘልቁ ዘንድ ረድተዋቸዋል። ሁሉንም ያስተሳሰረውና ያጋመደው ሀገራዊ ማንነትም ሆነ የኢትዮጵያዊነት አርማ የሆነው ሰንደቅ ዓላማ ተመልሰው ወደ ተራራው ጫፍ እንዲወጡ ያግዟቸዋል።

ወደ ዋናው ርዕሶች ለመግባት፣ በቅርቡ በአማራ ክልል ለተነሳው ህዝባዊ ጦርነት የገፋፉ መሰረታዊና ቅጽበታዊ ምክንያቶች ላይ እናተኩር።

**የፋኖ የእድገት ሂደት፣**

- ለ2010 ዓም ለውጥ መነሳትና መቀጣጠል ዋንኛው ኃይሎች የአማራው ወጣት፣ ፋኖና የኦሮሚያ ቄሮ ቢሆኑም፣ ሂደቱ ብዙም ሳይቆይ የአማራ ክልል ህዝብ ከታይታ ውክልና የዘለለ ተሳትፎ ተነፍጎ ከፖለቲካ ሂደቱ እንዲገለል ተደረገ፣
- ለኢህአዴግ 2 (ብልጽግና) መወለድ የአማራ ወጣቶች፣ ፋኖዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢያበረክቱም፣ በኦህዴድ የሚመራው የኦሮሞ ብሄረተኛ ኃይል የፖለቲካ ስልጣኑን ጠቀለለ፣
- በበርካታ የተለያዩ ቁልፍ መንግስታዊ የኃላፊነት ቦታዎች ኦሮሞዎች ተመደቡ፣
- የፌደራል መንግስቱ በአማራ ክልል አስተዳደር ውስጥ በተደጋጋሚ ጣልቃ ገባ፣
- እስከ ዛሬ ተድበስብሶ በቀጠለ መንገድ የእነጀነራል አሳምነውና የእነ ዶክተር አምባቸው ግድያ ተፈጸመ፣
- ያለክልሉ መሪዎች ፈቃድ የመከላከያ ኃይሉን ወደ አካባቢው በማስገባት በእምነት ተቋሞችና በዜጎች ላይ ኢሰብዓዊ የሆኑ ሰቆቃዎችንና ግድያዎችን ፈጸመ፣
- በየጊዜው፣ የክልሉ ፕሬዚዳንቶች ከቦታቸው እየተነሱ በምትካቸው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ደጋፊዎችና ታዛዦች ተሾሙ።
- በተጨማሪ፣ በተለያዩ እርከኖች ላይም ለጠቅላይ ሚንስትሩ ታዛዥ የሆኑ ግለሰቦች በመሾማቸው የክልሉ ባለሥልጣናት የጠቅላዩ ተላላኪዎች ተደርገው መታየት ጀመሩ፣
- የክልሉ ልዩ ኃይል እንደ ክልላዊ ተቋም በራሱ ዕቅድ እንዲጠናከር በመተው ፈንታ እንዲዳከም መደረጉና ሌሎች ጣልቃ ገብነቶች ችግሩን እያባባሱ ሄዱ።
- በአማራው ላይ በተሳሳተ ትርክት ላይ የተመሠረተ የበቀል ፖለቲካ (politics of venegence) የአገዛዙ ምልክት ሆነ።
- በ2013 ዓም ህወሃት በሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ ጥቃት በማድረሱ በተቀሰቀሰው ጦርነት ውስጥ የአማራው ክልል ልዩ ሃይል፣ፋኖና ሚሊሺያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢያበረክቱም፣ በፕሪቶሪያ፣(ደቡብ አፍሪቃ ውስጥ) በተደረገው ድርድርና ስምምነት አማራው እንደባይተዋር እንዲገለል ተደረገ። ለምዕራቡ ዓለም ፍላጎት ያጎነበሰ፣ አካታች ያልሆነ፣ ዘላቂ ሠላም የማያመጣና ጎጂ የሆነ ስምምነት መደረጉም ችግሩን አባባሰ። ይህም በ1983 ዓም በህወሃትና በደርግ መሀከል "የተደረገውን" ሳይካሄድ የጨነገፈውን የለንደኑን ስብሰባ ያስታውሳል።
- ወልቃይት-ጠገዴ-ጸለምትና ራያ ለህወሃት ተላልፈው እንዲሰጡ በህወሓትና በብልጽግና መሀከል የድብቅ ስምምነት መፈጸሙ ፍትህ-ፈላጊ የሆኑትን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣ በተለይም አማራውን፣ በጣም አስከፋ። የፌደራል መንግስቱ በኢትዮጵያ ላይ ደባ ፈጽሟል ብለው ብዙ ወገኖች እንዲያምኑ አደረገ።
- ህወሓት በብልጽግና ከተተካም በኋላ ፀረ-አማራና ፀረ-ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የሆነው ትርክት የመንግስትና የደጋፊዎቹ ቋሚ ፖሊሲ ሆኖ መቀጠሉ የአማራውን ስጋት ጨመረ።
- በኦሮምያ ክልል፣ በሙቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ አማሮች ላይ ዘርና ሃይማኖት ተኮር ፍጅት ተካሄደ። ከሞት የተረፉት ደግሞ ከመኖሪያዎቻቸው ቢፈናቀሉም ንብረታቸውን ቢቀሙም፣ ፌደራል መንግስቱ ጉዳዩን በተደጋጋሚ ባልሰማ/ባላየ እያለፈው ቀጠለበት። እንኳን ወንጀለኞቹን ለፍርድ ሊያቀርብ እስከናካቴው ስለፍጅቱም ሆነ ስለመፈናቀሉ ሳያነሳ ቀረ። ይህም፣ ፀረ-አማራና ፀረ-ኦርቶዶክስ ክርስትያን ወንጀለኛነትን ለሚጠራጥሩት ጭምር አረጋገጠ።
- ከ2013 ዓም ጦርነት ጋር ተያይዞ በአማራና በአፋር ክልሎች፣ ህክምና ተቋማት፣ ት/ቤቶች ፋብሪካዎችና ሌሎች የመሰረተ ልማት አውታሮች በህወሓት ሃይሎች ታቅዶበት ቢወድሙም፣ የፌደራል መንግስቱ ውድመቱን እንዳለየ/እንዳልሰማ አለፈው።

- በፌደራል መንግስቱ ትብብር ጭምር፣ በተዋህዶ ክርስትና ዕምነት ላይና በእስልምና ሃይማኖቶች ላይ የመከፋፈል፣ ጣልቃ የመግባትና ቤተ-ዕምነቶችንና ተቋማትን የማፍረስ እርምጃዎች በመወሰዱ በመንግስት ላይ የሚደረገው ተቃውሞ እየጨመረ እንዲሄድ አደረገ።
- አማራው ላይ ያነጣጠሩ እገታዎች መፈጸማቸውና መንግስት ጉዳዮን በዝምታ ማለፉ ብሶቱን ጨመረ።
- አማራው ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባና ምርቱንም እንዳያስገባ በተደጋጋሚ መከልከሉና የመሳሰሉ ጥቃቶች መካሄዳቸው የአማራውን ስሜት ጎዱ፣ አሳዘኑ። ከፍተኛ የመጠቃት ስሜት አሳደሩ።

በተጨማሪ፣

- ህወሃት በፕሪቶሪያው ስምምነት መሠረት ትጥቅ እንዲፈታ ሳይደረግ፣ እንዲያውም ወታደራዊ ሃይሉን በማጠናከር ወልቃይትን መልሶ ለመያዝ ዛቻና ሙከራ እያደረገ ባለበት ጊዜ፣ የአማራ ልዩ ኃይልን በማፍረስና በመበተን ፋኖን ትጥቅ ለማስፈታት ሙከራ ተደረገ፣ ይህም፣ ስር ሰዶ ለቆየው የአማራ ህዝብ ጥርጣሬ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሆነ። በህወሓት ስር ሲማቅቅ የኖረው የወልቃይት ጠገዴና ራያ ሕዝብ እንደተካደና ለከፋ ጥቃት እንዲጋለጥ እየተደረገ መሆኑን ተረዳ። ከዚያም፣ በፋኖና በልዩ ኃይሉ ስር የተደራጁ በርካታ ወገኖች ትጥቅ መፍታትን መቃወማቸውን መግለጽ ጀመሩ።
- በቀጣይ፣ የፌደራል መንግስቱ በጦርነት ልዩ ኃይሉን ለማጥፋትና ፋኖንም ትጥቁን ለማስፈታት ሙከራ ጀመረ፣ ትንኮሳዎችም አካሄደ፣ በዳባትና በደባርቅ እንዲሁም በወሎ የተደረጉ ሙከራዎችን መጥቀስ ይቻላል፣
- የመጀመሪያ ሙከራዎቹ ከሸፉ። ግን ሂደቱ በዚያ አልቆመም። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አሁናዊው የኢትዮጵያ ሁኔታም ለብሶቱና ለጦርነቱ ከዋነኛ ታሳቢዎች መሀል ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል፣
- በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞችም ዜጎች በአማራነታቸው እየተለቀሙ በመታሰር፣ በመደብደብና በመሠቃየት ላይ ናቸው፣
- በተወሰኑ አካባቢዎች፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ መንቀሳቀስ አደገኛና አስፈሪ ሆኗል። ዛሬ ማንኛውም አማራ በኦሮምያ ውስጥና በሌሎች ፌዴራል መንግሥቱ በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች በመንገድ ላይ ምን ሊገጥመው እንደሚችል መገመት እንኳን አይቻልም። በጥቅሉ ሰላም ከሀገሪቱ ከኮበለለች ጊዜው ረዝሟል።
- ፋኖ የትጥቅ እንቅስቃሴ ከጀመረ በኋላ፣ በአማራ ክልል በየደረጃው የሚገኙ የብልጽግና አመራር መንግሥታዊ አስተዳደሮች ፈራርሰዋል። አሉ ከተባለም ምንም መፈየድ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።
- የአገዛዙ ምርኩዝ የነበረው የአማራ ክልላዊ መንግስት እንዳያንሰራራ ሆኖ ፈራርሷል፣ እናም አካባቢውን መቆጣጠር አዳግቶቷል፣
- በመላ የአማራ ክልል ታጣቂው ኃይል የወታደራዊ የበላይነትን ይዟል፣ በርካታ የገጠር አካባቢዎችን ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራልም። ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ከፋኖ ኋላ ተሰልፏል፣መከላከያ ኃይሉ ያለ ርህራሄ ዜጎችን በመግደልና በመኖሪያ ቤቶችና ተቋማት ላይ በከባድ መሣሪያና በድሮን ጭምር ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ፣ ፋኖዎች ወደ ገጠሮች ሲወጡ፣ አንዳንድ ከተሞችን መከላከያ መልሶ ተቆጣጥሯል፣ ግን በሂደት የፋኖዎች መመለስም ስለሚኖር ሁኔታው ገና አልለየለትም፣
- የፋኖን ድል አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በበጎ ዓይን አይቶታል፣ ትኩረትም ሰጥቶታል።
- ፋኖ፣ ለቀጣይ የውጊያ ዙር የሚረዳው በርካታ መሳሪያና ተተኳሾችንም፣ እንዲያጠቃው ከተላከው የመከላከያው ተማራኪዎችና በፈቃደኛነት ከሚቀላቀሉት በመሰብሰብ አከማችቷል፣
- ፋኖ እስከዛሬ ባደረገው ትግልና በከፈለው መስዋዕትነት እንዲሁም ባሳየው ሥነ ምግባራዊና ፍትሃዊ አያያዝ ዓለም አቀፋዊ ትኩረት ስቧል።
- ፋኖ ከርቀት እንደሚታየው፣ ለተለዋዋጭ ሁኔታ ቀልጣፋ መልስ የመስጠት አቅሙ እስከአሁን ያገኛቸው ድሎችን የማስጥበቅ አቅም እንዳለው ያስረዳል፣
- በሁኔታዎች አስገዳጅነት ጦርነት ውስጥ የገባው ፋኖ፣ በጊዜ ሂደት የፖለቲካና የወታደራዊ አመራር ብቃቱ እየጨመረ መሄዱን መገንዘብ ይቻላል፣
- በውጭ ሀገራት የሚገኙ በርካታ የሚድያ አካላት ስለ ፋኖ ትግልና እንቅስቃሴ ይዘግባሉ። በርካታ ኢትዮጵያውያን ስብስቦችና ግለሰቦችም ፋኖን በማገዝ ስራ ላይ ተሰማርተዋል፣
- የፋኖን ትግል ሀገራዊ ገጽታ የሚያመላክቱ ገለጻዎች በፋኖ መሪዎች ከመስጠታቸውም በተጨማሪ፣ ሀገራዊ አቃፊነትን የሚገልጹ ተግባራዊ ጥረቶችም እየተደረጉ መሆናቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ።

በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ተገፋን የሚሉ ዜጎች ፋኖን እንደቤዛቸው መቁጠር ጀምረዋል። እነሆ፣ ኢትዮጵያ ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ በወፍ በረር መልክ ዳሰሳ አደረግን። በቀጣይ፣ ስለአለፉት በርካታ ዓመታት ትንሽ እንበል።

## በኢትዮጵያ ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችና ያመለጡ ዕድሎች

ለኢትዮጵያ ችግሮች ዋና ዋና መንስዔዎቹ ሶስት የተያያዙ ምክንያቶች ሆነው እናገኛለን። እነሱም፣ ህገ መንግስታዊ፣ መዋቅራዊና ሥርዓታዊ ናቸው። እነዚህ ሶስት ምክንያቶች ተወራራሽና የማይነጣጠሉ ሲሆኑ፣ በዚህ ዝግጅት ዐበይት በሆኑና በመከኑ ሥርዓታዊና መዋቅራዊ ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን፤ በየዘመኑ ታሪክ የቸራቸው ዕድሎች ዕውን ሳይደረጉና ጥቅም ላይ ሳይውሉ በመቅረታቸው ከውድቀት አዙሪት መውጣት አልተቻለም። እነዚህን የመከኑ ዕድሎች ተራ በተራ እንመልከት።

### ዕድል 1 - የታህሳስ 1953 ዓም የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ

በ1953 ዓም የተካሄደው የእነ ጀነራል መንግስቱ ነዋይ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ፣ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንበርን ቢነቀንቅም፣ ሀገሪቱ ለውጥ እንደሚያስፈልጋት የሚያበስር ጥሪ፣ ደወል ነበር። ኢትዮጵያ ለእድገቷ ጋሬጣ የሆነባት አንድ ወጥ (unitary monarchy/government) የዘውዳዊው ሥርዓት ቁንጮ ተነስተው በህገ-መንግስታዊ (constitutional monarchy) የዘውድ አገዛዝ መተካት አለበት ተባለ። ደም ፈሰሰ። በርካታ ባለሥልጣናት ያለፍትህ ተገደሉ። አካታች ሥርዓት እንዲወለድ የሚጣራው ደውልም ማስተጋባቱን ቀጠለ። ንጉሡ ግን ጥሪውን ሳይሰሙ ቀሩ። ወይም ሊሰሙት አልፈለጉም። ምናልባት ደውሉን አልሰሙ ይሆናል ብለው በማሰብ፣ ለዘውዱ ቅርብ የሆኑ እንደ አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ፣ ጀኔራል ዐብይ አበበ፣ አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄና ሌሎች ባለሥልጣናት ንጉሱን አሳሰቧቸው። እንደ አሜሪካ የመሳሰሉ ለንጉሱ ቅርብ የሆኑ መንግስታትም ለውጥ እንዲያደርጉ ምክረ-ሃሳቦች አቀረቡ። ወደ አማርኛ መቼ እንደተተረጎመ ባይታወቅም፣ “ፍሬሬ ጃኮብ” የተባለ የፈረንሳይኛ መዝሙርን ተማሪዎች ይዘምሩ ጀመር። ትርጉሙ፣ “ወንድሜ ያዕቆብ፣ ወንድሜ ያዕቆብ፣ ደውል ተደወለ፣ ተነሳ፣ ተነሳ” የሚል ነበር። ሆኖም፣ ሁኔታዎች በፊት በተቀደደው ቦይ መፍሰሳቸውን ቀጠሉ። ለውጥ ጠፋ። ደውሉም ለአስራ ሶስት አመታት ያህል አቃጨለ። እነሆ ኢትዮጵያ አመርቂና ዘልቄታዊ የሰላምና የዕድገት የመጀመሪያ ዕድል አመለጣት።

### ዕድል 2 - የ1966 ዓም ሕዝባዊ አመጽና የልጅ እንዳልካቸው መኮንን ሹመት

ደውሉ ወደ አታሞነት ተቀይሮ ህዳር 1966 ዓም በመላ ሀገሪቱ ተሰማ። የታህሣሥ መፈንቀለ መንግስት ሙከራ ከተካሄደ ከ13 ዓመታት በኋላ የ1966 ዓም ሥር ነቀል አብዮት ፈነዳ። ተማሪው፣ ሠርቶ አደሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ታክሲ ነጅው፣ ተራው ወታደርና የበታች መኮንኖች፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ ክርስቲያኑ ሙስሊሙ፣ በዘር በሃይማኖት ሳይከፋፈል፣ እንደ አንድ ሕዝብ ጉልበቱን አጽንቶና ተሞ ሰላማዊ ትግሉን አቀጣጠለ። ሁሉም ተነሳ፣ ተነሳሳ። ዲሞክራሲ ይከበር፣ መሬት ለአራሹ ይመለስ፣ በብሔር፣ በፆታ፣

በሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሠረቱ ጭቆናዎች ተወግደው፣ በሕግም በተግባርም እኩልነት ይረጋገጥ፣ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት፣ የሚዲያ ነፃነት በሕግ የፀናና ተግባራዊ ይሁን የሚሉትንና የመሳሰሉ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች አንግቦ ታገለ።

ዕድሜ የተጫናቸው ንጉስም ከገቡበት ሰመመን ባነኑ፣ ግን ረፍዷል። ሥርዓቱ መፈረካከስ ጀምሯል። የአቶ አክሊሉ ሃብተወልድ ካቢኔ ፈርሶ የሥርዓቱ ልጆች ከሆኑት መሀል አንዱ፣ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን መንግስት እንዲመሰርቱ ታሰበ። ያም ሆነ። አዲሱ መንግስት የሕዝቡን ስሜት የሚመጥንና አካታች አልነበረምና፣ “ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም” የሚል መፈክር ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ተናኘ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች ማህበርም፣ አካታች የሆነ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ይቋቋም የሚል መሪ ሃሳብ አነሳ።

በአጭር ጊዜ ቆይታቸው ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፣ የፀጥታ ኮሚሽን የሚል ተቋም መስርተው ለወራት ለውጥ እንዲመጣ ሲታገል በነበረው የማህበረሰብ አካል ላይ በትር አሳረፉ። ያ እርምጃም፣ መጥፊያቸው ሆነና በቅጽበት እንደመጡ ሁሉ በቅጽበት ሄዱ። አሁንም ሁለተኛው ዕድል አመለጠ።

## ዕድል 3 - ንጉሱ ወረዱ፣ ደርግ ስልጣን ቀማ

በ1966 ዓም ሰኔ መጨረሻ ላይም የለውጡ አካል የነበረውን ወታደር ተገን አድርጎ ደርግ የተባለ አካል የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ ተቃውሞ በመጥለፍ መንግስት ማስተዳደር ጀመረ። ከሰኔ እስከ መስከረም ባለው ጊዜ ውስጥም መሰናዶ ሲያደርግ ቆይቶ መስከረም 2 ቀን ንጉሱን ከሥልጣን አወረደ፤ ህገ መንግስቱን ገድቦ፣ ለበርካታ አመታት ኢትዮጵያ በአዋጅ እንድትተዳደር አደረገ።ፓርላማውን በተነ። መናገር፣ መሰብሰብ፣ መጻፍ፣ ወዘተ፣ እንደ ወንጀል ተቆጥረ፣ ለእስራትም ሊዳርጉ እንደሚችሉ አዋጅ ወጣ።

ብዙም ሳይቆይ፣ ያለምንም የፍርድ ሂደት የቀድሞ ባለሥልጣናትን በርሸና ረፈረፈ። በደርግ ወስጥ የነበሩ ተቀናቃኞችን ተራ በተራ ከመነጠረ በኋላ ኮለኔል መንግሥቱ ሀይለማርያም ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ የሆነ አምባገነን ሆኖ ወጣ። በመቀጠል፣ የፖለቲካ ድርጅቶችን የቀይ ሽብር በሚል ዘመቻ ካፈረሰ፣ አባላቱን በጅምላ ከፈጀና ለእሥራት ከዳረገ በኋላ አያሌ መስዋዕትነት የተከፈለበት የለውጥ ዕድል ገደል ገባ።

ለ17 ዓመታት የዘለቀው የደርግ አገዛዝ አገሪቱን ለከፋ ጦርነት፣ ርሐብና ስደት ዳረገ። ከሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ ወደ ጎረቤት አገሮች ሲሰደድ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ በኢሰብዓዊ ሰቆቃና ግድያ፣ በረሐብና በጦርነት ረገፉ።

በአጭሩ፣ አካታች ሥርዓት ለመመስረት ተከፍቶ የነበረው ሸንቁር ዳግመኛ ተደፈነ። የዲሞክራሲ ጭላንጭል ከኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ብን ብሎ ጠፍቶ በነፍጥ መፈታተን ተጀመረ። የወታደራዊ መንግስቱ ሥልጣን ላይ በቆየበት ዘመን፣ በምዕራቡ ዓለም የሚደገፉ ጠንካራ ብሄረተኛ ኃይሎችና ከሀገራዊው የፖለቲካ ተሳትፎ የተገፉት ኅብረብሔራዊ ሃይሎች ተፈታተኑት። ያ ጦስ ዛሬ ድረስ ዘልቆ የኢትዮጵያን ዕድል ፈተና ውስጥ ከተተ። በህዝብ ትግል የመጣው ትግል በደርግ ተጠልፎ የህዝቡን ዕድል ለሶስተኛ ጊዜ አከሸፈ።

## ዕድል 4 - በ1969 ዓም በደርግ ውስጥ የተነሳው የለውጥ እንቅስቃሴ

በ1968-69 ዓም ላይ ቁጥራቸው ከመቶ በላይ በሚሆኑ የደርግ አባላት መሀከል ልዩነት ተነሳ። መንስዔውም፣ በዚያን ጊዜ ሻለቃ የነበሩት መንግስቱ ሃይለማርያም ስልጣን እየጠቀለሉ ከመሄዳቸው ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ "...የልባችንን ለመናገር ፍርሃት አድሮብናል።...ሻለቃ መንግስቱ አምኖበት ያመጣውን ሁሉ በግድ እንዲወሰን ያደርጋል። የሥራ ክፍፍል የለም።ሥራው ሁሉ ሻለቃ መንግስቱ ላይ ተደራርቧል" ሲል አተተ (የደርግ ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ ጉባዔ - 4ኛመዝገብ ገጽ 30-88) የአንድ ሰው የፈላጭ ቆራጭነት ሚና እየጎለበተ ሄዶ በ1968 ዓም መጨረሻ ላይ የደርግ መሪ አባላት ከነበሩት ሁለቱ በሻለቃ መንግስቱ ብቸኛ ትእዛዝ ተገደሉ። በኤርትራ የ2ኛው ክፍለ ጦር አዛዥም ተመሳሳይ ዕጣ ገጠማቸው። ከእነዚህ ባለሥልጣናት ጋርም ሌሎች 21 ሰዎች ኮተቤ አካባቢ ተወስደው ተረሸኑ። (ደም ያዘለ ዶሴ፣ ግድያ 6 ክስ 6) በዚሁ ወቅት፣ ደብረ ዘይትና አስመራ የነበረው አየር ወለድ አምጾ ውጥኑ ሊሳካለት ስላልቻለ ተበተነ፣ ፈራረሰ። አየር ኃይልም አመጽ አካሄደ።

ችግሩ እየበረታ ሲሄድ፣ በሐምሌ ወር 1968 ዓም በተደረገ ስብሰባ፣ "የሲቪል መንግስት የሚቋቋምበትን መንገድ የሚጠቁም የመንደርደሪያ ሃሳብና በደርግ ውስጥ የተፈጠረውን ቀውስ የመፍቻ ብልሃት ይዞ እንዲመጣ" በሚል እሳቤ 15 የደርግ አባላትን ያሳተፈ ኮሚቴ ተቋቋመ። የዚህ ኮሚቴ አባላት "...የብዙሃኑ ምናልባትም 75% (ሰባ አምስት በመቶ)" ሊሆን የሚችል የደርግ አባላት ድጋፍ ነበራቸው። (ፍቅረ ስላሴ፣ እኛና አብዮቱ፣ ገጽ 306፣ 2006 ዓም) በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ሻለቃ መንግስቱና ሻለቃ አጥናፉ ያልተካተቱ ሲሆን፣ እነሻምበል ሞገስ፣ መቶ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ፣ ጀነራል ተፈሪ በንቲና ሌሎች አባላት ለውጡን ሊያመጡ የሚችሉ ሰነዶች፣ መመሪያዎች፣ ወዘተ፣ ሲያዘጋጁ ቆይተው የመፍትሄ ሃሳቦቹን ለደርግ ጠቅላላ ጉባዔ አቅርበው በአብዛኛው አባላት ተደገፉ። በዚህ ውሳኔ የደርግን ድጋፍ ያጡትና ሥልጣናቸው የተገደበው ሻለቃ መንግስቱ ስለሚወስዱት የበቀል እርምጃ ማሰላሰል ጀመሩ።

አዲስ አበባ የሚገኘው የ4ኛ ክፍለ ጦር በደርግ ውስጥ የተጀመረውን እንቅስቃሴ ይደግፉ የነበሩት ሻለቃ አጥናፉን ለደርግ አባልነት የመረጣቸው ተቋም ከመሆን ባሻገር ደጋፊያቸውም ነበር። እናም፣ ሻለቃ መንግስቱ የደርግን የሪፎርም እንቅስቃሴ ለመግታት ሲነሳሱ የ4ኛው ክፍለ ጦር ሊተባበራቸው እንደማይችል በመረዳታቸው የቤተ መንግስት (የደርግ) ጠባቂ በሆነውና ጥቂት ወታደሮች ባሰለፈው ኃይል ላይ ትኩረት አደረጉ። ይህን ኃይል ይመራ የነበረው የሻለቃ መንግስቱ የቅርብ ወዳጅና የፖለቲካ ሸሪካቸው ኮሎኔል አስፋው በመሆኑ

ውጥኑን በስራ ለመተርጎም አዳጋች አልነበረም። እናም፣ ጥር 26 ቀን 1969 ዓም ጀነራል ተፈሪ በንቴ፣ ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል፣ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌና ሌሎች 4 የኮሚቴው አባላት ከደርግ ስብሰባ ላይ እየተጠሩ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ተረሸኑ። የሻለቃ መንግስቱ ቡድንና ተባባሪ የፖለቲካ ድርጅቶችም ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገርን ሲሉ መግለጫ አወጡ። ከዚህ በኋላ ነበር በኢጣልያን ጦርነት ጊዜ እንደተደረገው የብዙ ወጣቶች ህይወት በግፍ የተቀጨውና ደማቸው በየአደባባዮቹና በየመንገዱ እንዲፈስ የተደረገው። ኢትዮጵያም በሶቭየት ሕብረት ስር በመውደቋ የቀዝቃዛው ጦርነት አካል ከመሆኗ ባሻገር፣ ኢትዮጵያን ከወታደራዊ ወደ ሲቪል፣ ምናልባትም ወደ ዲሞክራሲያዊና አካታች ጎዳና ሊወስድ ይችል የነበረ ሌላ ዕድልም መከነ።

## ዕድል 5 - ደርግ/ኢሰፓ ተወግዶ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ኢህአዴግ ሥልጣን ያዘ

በ1983 ዓም ለኢትዮጵያ ሌላ የመንግስት ለውጥ፣ ሌላ ዕድል ቢቸራትም አጋጣሚው የተጨናገፈው ገና ጠዋት ላይ ነበር። በአሜሪካ መንግስት አስተባባሪነት ለንደን ከተማ ላይ ብሄረተኛ ኃይሎችን ብቻ ያሳተፈ ስብሰባ ተደርጎ መጪው የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ተወሰነ። ኢትዮጵያ በብሄረተኛ ኃይሎች እጅ እንድትወድቅ በአሜሪካና በእንግሊዝ ቡራኬ ሲሰጥ የውጭ ኃይሎች የረዥም ጊዜ እቅድ ሰመረ። እንደተፈራው፣ ልዩነትን፣ ክፍፍልንና ጥላቻን በኢትዮጵያውያን መሐል በመዝራትና ወገንን በመነጣጠል ሕዝብ ለሕዝብ የሚያባላ ጦርነት እንዲያቆጠቁጥ በር ከፈተ።

በግንቦት ወር 1983 ዓም ሕወሓት ለይስሙላ ከፈጠራቸው የብሔር ድርጅቶች ጋር በመሆን ኢህአድግ በሚል ስያሜ እንደ ደርግ ሁሉ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶችን አግልሎ ሥልጣኑን በሞኖፖል ያዘ። ኦነግ (OLF) ለአንድ ዓመት ያህል የኢህአዴግ ሽርካ ሆኖ ሰራ። የአገሪቱ መመሪያ የተባለ ቻርተርና፣ ሕዝቡን በብሔረሰብ የሸነሸነ ህገ መንግሥት አረቀቁ፣ ቋንቋን መሠረት ያደረገ ድንበር አካለው፣ ሕዝቡን እርስ በእርሱ የሚያናክስ፣ በአወቃቀርም ሆነ በአሥራር ፍፁም ከዴሞክራሲ የራቀ ፌዴሬሽን አዋቀሩ። ነባር ድርጅቶችም ሆኑ የኢህአዴግ አባል ያልሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ገሚሶቹ ሀገር እንዳይገቡ ተከለከሉ። ደፍረው የገቡትም ታሰሩ፣ ተሳደዱ። የአማራው ማህበረሰብም በዚህ ሂደት ውስጥ በቀጥታ እንዳይካፈል ዕድል ተነፈጎት በምስለኔዎች እንዲተዳደር ተደረገ።

ለ27 ዓመታት ሕወሓት (TPLF) እንደልቡ የሚያሽከረክረው ኢህአደግ ሥልጣን ላይ የቆየ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በታሪክ ታይቶ በማይታውቅ ደረጃ፣ መጠንና የጊዜ ርዝመት በመላው ሕዝብ ላይ ግፍና በደል፣ እንዲሁም ዝርፊያ ተፈፀመበት። ከፋፍሎ የመግዛት ብቻ ሳይሆን፣ አበጣብጦ የመለያየት ርዕዮት ሰርጎ እንዲያረሰርሰው በማድረግና ሀገራዊ አመለካከትና የፖለቲካ ቅኝት ያላቸው ተቃዋሚዎች ያለምንም የፍርድ ሂደት ለእሥራት፣ ለስቆቃና ለግድያ ተዳርጉ።

በእነዚህ አመታት፣ የተተኪ ትውልዱን አእምሮ ለመቆጣጠር በማሰብ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የተመረቁ ካድሬዎች ሲቪክስና የተፈበረከውን ታሪክ ማስተማር ጀመሩ። የ3ሺህ አመት ባለታሪክ ከተባለችው ከአክሱም በስተቀር ኢትዮጵያ የ150 አመት እድሜ ያላት፣ በአፄ ምንሊክ ተጠፍጥፋና ተጨፍልቃ የተገነባች ሀገር ናት ተብሎ ተሰበከ። በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ከአንድነታቸው ይልቅ ልዩነታቸው ጎልቶ ተስተማረ። በተገኘው አጋጣሚም፣ በየክፍላቸውም ሆነ ከዚያ ውጭ ተማሪዎች በቋንቋና በብሔረሰባዊ ማንነታቸው ላይ ተመሥርተው እንዲደራጁ ተደረገ። ኢትዮጵያዊ ዜግነትም ሆነ ሌሎች የማንነት መገለጫዎች ሥፍራ አጡ። የህወሃት የፖለቲካ መስመር በየት/ቤቶቹ ተሰበከ። ያልተፃፈበት የአእምሮ ሰሌዳ ይዘው የገቡ ተማሪዎችም፣ ውሱን፣ የቋንቋና የብሔረሰብ ማንነት ላይ ብቻ የተመሰረተውን አደገኛና መርዘኛ ትምህርት ቀሰሙ። ዛሬ በየክልሉ የምናያቸው አብዛኞቹ ባለሥልጣናት፣ ወያኔ ሀርነት ትግራይ በዘረጋው የትምህርት ካሪኩለም ታንጸው የተቀረጹና ህወሓት የዘራው የነጠላ ማንነት ፖለቲካ ብቸኛውና ትክክለኛው አማራጭ ነው ብለው የሚያስቡ ናቸው። ወዲያም አለ ወዲህ፣ ኢትዮጵያ መፃኢ ዕድሏን የተቃና ሊያደርግላት የሚችል አራተኛውን ዕድል ተነፈገች።

## ዕድል 6 - የ1997 ዓም ምርጫ - ሌላ ታሪካዊ ዕድል

በ1997 ዓም አካታች መንግስት ይመሰረት ዘንድ ታሪክ አንድ ሌላ ዕድል ይዛ ብቅ አለች። የኢህአዴግ መንግሥት ኢትዮጵያውያን ለመንግሥቱ ያላቸውን የጥላቻ ደረጃ ካለመረዳትና በወቅቱ ከውጭ መንግሥታትም ከተደረገበት ጫና ምክንያት የፖለቲካ ምህዳሩን ላላ በማድረጉ በተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች ሰፋ ያለ የምርጫ ቅስቀሳ፣ ዝግጅት፣ ድርጅት፣ ወዘተ፣ ተካሂዶ ምርጫ ተደረገ። የኢትዮጵያ ሕዝብ "ሕዝበ-ውሳኔ" በሚመስል መልክ ለተቃዋሚ ኃይሉ ሰፊ ድጋፍ ሰጠ። ቅንጅት አዲስ አበባን በምርጫ አሸነፈ። በተለያዩ ክልሎችም የማይናቅ ድል ተጎናጸፈ። እንደ በፊቶቹ ምርጫዎች ሁሉ በዝረራ አሸንፋለሁ ብሎ ይገምት የነበረው ህወሃት፣ የቆመበት መሬት እየከዳው

ሲሄድ፣ ለሁኔታው ያልተዘጋጀው ይህ ድርጅት ጠመንጃን እንደ መላ ዘየደ። በደቦ በሚመስል ሁኔታ የተደራጀው ተቃዋሚም የህወሃትን ሸፍጥ፣ ደባና እመቃ መቋቋም አልቻለም። ኢህአደግ የምርጫ ውጤቱን በአደባባይ ዘርፎ የቅንጅትን አመራር በጅምላ እሥር ቤት አጎረ። ይህን ኢዴሞክራሲዊ አድራጎት ለመቃወም አዲስ አበባ ውስጥ ሰላማዊ ሰልፍ ባደረገው ሕዝብ ላይ ኢህአደግ ተኩስ ከፍቶ ከ200 በላይ ንፁሐንን ገደለ፣ በተጨማሪ በርካታዎችን አቆሰለ። ገሚሱ ከሀገር ኮበለለ፣ ሌላው ከስራው ተባረረ።

አምባገነኑ የኢህአዴግ አስተዳደር በየጊዜው የተነሳበትን ተቃውሞ ለማዳፈን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በጠቀለላቸው በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በፀለምትና በራያ በርካታ አማራዎችን ከመፍጀቱም በተጨማሪ ብዙዎችን ለአካላዊ ጉዳት፣ ለእሥራት ዳርጓል። ከኑሮዋቸው አፈናቅሎ፣ ለስደት የዳረጋቸው ከ500,000 በላይ ይሆናሉ። በጋምቤላ የተነሳበትን ተቃውሞ ለማብርድ የአንድ መንደር ኗሪዎችን አጥቅቶ ከ480 በላይ የሚሆን ሕዝብ ፈጅቷል። በሱማሌ ክልልም ተቃውሞውን ለማዳፈን አያሌ የእሥራት፣ የግድያና የማሳደድ ወንጀል ፈፅሟል። ያም አለ ይህ፣ እንደገና ኢትዮጵያ ስድስተኛው ዕድል አመለጣት።

### ዕድል 7 - የ2010-11 ዓም የቄሮና የፋኖ አመጽ

በህወሃት የሚመራው ኢህአድግ ከሥልጣን ከመወገዱ በፊት፣ ከሁለት ዓመት ተኩል በላይ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ የኦሮሚያ ቄሮዎችና የአማራ ክልል የፋኖ ወጣቶች ባካሄዱት ትግል በጅምላ እሥር ቤት ተወረወሩ። በገፍና በግፍ በርካቶች ተገደሉ። ይህ ከልክ ያለፈ የኢህአዴግ የግፍ አገዛዝ ገድቡን አልፎ የግፍ-ጽዋውም ሞልቶ ሲፈስ በህወሃት በሞኖፖል የተያዘው ሥልጣን አብቅቶ፣ በድርጅቱ ውስጥ የፖለቲካ ግብግብና መከፋፈል ተቀሰቀሰ።

በዚህ ግርግር መሀል፣ የኦሮሞና የአማራ ወጣቶች የጀመሩትና ያካሄዱት መጠነ-ሰፊ እንቅስቃሴ፣ ኢ.ፒ.ዲ.አ. ውስጥ በተፈጠረው፣ በኢህአዴግ 2ኛ ተጠለፈ። በወቅቱ በተደረገ ምርጫም፣ ዓብይ ጠ/ሚኒስትር ሆኑ። የጠ/ሚኒስትር ዓብይና የአቶ ለማ ቲም “ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ” በሚሉና በመሳሰሉ አስመሳይ መፈክሮቻቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ አማለሉ፣ አታለሉ።

በህወሓት ይመራ የነበረው ኢህአዴግ 1ኛ ከሥልጣን ወርዶ በኦህዴድ፣ በኋላ ብልጽግና በሆነው፣ በኢህአዴግ 2ኛ ሲተካ፣ አካታች መንግስት ለመመስረት የነበረው ዕድል እንደመከነ ውሎ አድሮ ግልጽ ሆነ። የኢህአዴግ 1ና የኢህአዴግ 2 ልዩነት የህወሃት ከግንባሩ መወገድ ሲሆን፣ የኢህአዴግ 1 ዋነኛ መለያ የነበረውና የሆነው በቋንቋና ብሄረሰብ ላይ ያጠነጠነ የማንነት ፖለሲ ኢህአዴግ 2ትም እጅግ በከፋና አሰቃቂ በሆነ መልኩ አስቀጠለው። በኢህአዴግ 1 ዘመን አማራው ላይ የተጀመረው ግፍ፣ ነብስ ዘርቶና ስጋ ለብሶ የዘር ፍጅት አደጋንም ጭምር አንግቦ መጣ። በመቶ ሺህዎች ተፈናቀሉ። ተገደሉ። ቤታቸው ፈረሰ። በኢህአዴግ 1 ወቅት ህወሃትና ከፍተኛ ባለሥልጣናቱ የሀገሪቱ ዋነኛ የሀብት ተቀራማቾች የነበሩ ሲሆን፣ በብልጽግና ጊዜ በኦሮሙማ ተተኩ።

በ2013 ዓም ምርጫ ቢካሄድም፣ ግዙፍ የሆነ የህብረተሰብ ክፍልን አገለለ። በትግራይ፣ በኦሮምያና በአማራ ክልሎች ምርጫው አልተካሄደም ወይም በከፊል ነበር የተካሄደው፣ በተካሄደባቸው ቦታዎችም ሂደቱ ከፍተኛ ቅሬታ ያስነሳ ሆኖ ነበር። እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ተደማምረው በተለይ ለአማራ ብሄረተኝነት ማቆጥቆጥና ነብስ መዝራት ምክንያት ሆኑ።

ይባስ ብሎም፣ ከ20 ዓመታት በላይ ድንበር ሲጠብቅና የትግራይ ሕዝብን ሲያገለግል በኖረው የሰሜን ዕዝ ላይ የህወሃት መሪዎች ያካሄዱት ፍጅት ረጅምና ከባድ ጦርነት ቀስቅሶ፣ በአማራ፣ በአፋርና በትግራይ ከ1 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ ሕይወቱን ተነጠቀ። በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ቆሰሉ፣ ንብረታቸው ወደመ፣ ከኑሯቸው ተፈናቀሉ። በዚህ ጦርነት ውስጥ በጋራ የተካፈሉ የሀገር መከላከያ፣ የአማራ ክልል ልዩ ኃይል፣ ሚሊሺያና ፋኖ፤ የአፋር ልዩ ኃይልና ሚሊሽያ፣ እንዲሁም ከሌሎች ክልሎች የተውጣጡ የልዩ ኃይሎች አባላት፣ በአገር የማዳን ርብርቦሽ ተሰማርተው የህወሃት መሪዎችንና ጦራቸውን ሽንፈት ግተው የማያዳግም ድል አበሰሩ። ከህወሓት ጋር በተደረገው ጦርነት እንዲደራጅ፣ እንዲታጠቅና ከመንግስት ጎን እንዲሰለፍ እድል ያገኛው የፋኖ ኃይልም በጊዜ ሂደት በምርኮ ትጥቁን አሻሻለ፣ ጉልበቱን አፈረጠመ።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ በሀገራዊ መከላከያ ላይ ክህደትና ጥቃት የፈፀሙ የህወሃት መሪዎች የሚገባቸውን ፍርድ ሳያገኙ በፕሪቶሪያ የሰላም ድርድር ላይ በተፈጠረ ግልጽነት የሌለው ስምምነት አማካኝነት ያለምንም ተጠያቂነት አምልጠው፣ ተደረገ የተባለውን የሰላም ስምምነትም በጣሰ ሂደት ተመልሰው ሥልጣን ያዙ፣ እንዲያውም ተሸለሙ።

በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ዘመን፣ ችግሩ ተባብሶ፣ በሰሜኑ ጦርነትም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች 4.5 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ከኑሮው ተፈናቅሎ፣ በአማራ ክልል፣ በአፋርና በትግራይ በቂ መጠለያና በቂ የቀን ጉርስ ሳያገኝ የሚያዋትት ኑሮ ይገፋል። በዚህ የሕዝብ መፈናቀል የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አፍጋኒስታትንንና ሶሪያን ከመሰሉ በጦርነት ከታመሱና ከደቀቁ አገሮች ጋር ትመሳሰላለች።

ጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ ሥልጣን ከያዙበት ወቅት ጀምሮ ዘር-ተኮር ግድያ ኦሮሚያ በሚገኘው የአማራ ብሔር አባላትና፣ በኦርቶዶክስ ክርስትና ዕምነት ተከታዮች ላይ የተካሄደ ሲሆን፣ ያለቀውንና ንብረቱን ተነጥቆ የተፈናቀለውን ቤቱ ይቁጥረው ማለት ይቀላል። አዲስ አበባን የሚከብ ግዙፍ (ሜጋ) የሸገር ከተማ ለኦሮሚያ እንመሰርታለን በሚል ሰበብ፣ የአዲስ አበባን ኗሪ ከማስጨነቃቸውም በላይ በከተማዪቱ አንድ መቶ አስር ሺ (110, 000) የሚሆኑ ቤቶች ሲፈርሱ፣ እናቶችና ሕፃናት ሳይቀሩ ለአውሬ ተዳርጉ። በሌሎች የኦሮሞ ከተሞች ከተፈናቀሉት ጋር ተደምሮ ከ500,000 ሺህ በላይ የሚሆኑ በአብዛኛው የአማራ ብሔረሰብ አባላት የዚህ ግፍና ወንጀል ሰለባ ሆነዋል። አብዛኛዎቹ ሴቶችና ሕፃናት ናቸው። አዛውንትንም ይጨምራል።

ከደሴ፣ ከጎጃምና ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ ለንግድም ሆነ ለሕክምና ወይም ዘመድ ጥየቃ ለመግባት ሲሞክሩ በአዲስ አበባ መግቢያዎች ላይ በኦሮሚያ ደህንነትና ፖሊስ መታወቂያቸው እየተፈተሸ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አማሮች ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደርገዋል። በነፃ የመንቀሳቀስ የዜግነት መብታቸውን የመነጠቅ ወንጀል ተፈፅሞባቸዋል። እስከዛሬ ወንጀሉ እየተፈጸመባቸው ነው።

ይህ አልበቃ ብሎ፣ የጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ መንግሥት ልዩ ኃይሉን፣ ሚሊሺያውንና ፋኖን ትጥቅ አስፈታለሁ በሚል ትዕቢት የአማራን ክልል ወሮ መጠነ ሰፊ ጦርነት አካሄደ። ይህ ሁሉ የሚከናወነው ትጥቁን ሙሉ በሙሉ ያልፈታው የህወሃት ጦር ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ገና በአማራው ክልል ላይ እያንዣበበ በነበረበትና ባለበትም ሁኔታ ነው። ይባስ ብሎ አማሮች በሚሳደዱበት በኦሮምያ ክልልም፣ ልዩ ኃይሉ ተጨማሪ ወታደር በገፍ እየመለመለ፣ እያሰለጠነና እያስታጠቀ ነው። ወዲያም አለ ወዲህ፣ አሁንም ኢትዮጵያ ሌላ ዕድል አመለጣት።

### ዕድል 8 - ሌላ ታሪካዊ አጋጣሚ - የፋኖ የትግል ሚና

ዕድል 7 እንዲወለድ ምክንያት የሆነው የአማራ ወጣቶች ስብስብ የሆነው ፋኖ፣ እንደ አንድ የለውጥ ሃይል በትግሉ ቢሳተፍም፣ በኦህዴድ ተገፍትሮ ከሂደቱ በመወገዱ ብቻ ሳይሆን፣ በህወሃት ዘመን የተጀመረው ፀረ-አማራ ትርክትና ጥቃት በመቀጠሉም ጭምር ነበር። ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የጦርነቱ ቀስቃሽና የውድመትና ጥፋቱም ዋነኛው አድራሽ የሆነው ህወሃት፣ከብልጽግና ጋር በመመሳጠር ትጥቅ ሳይፈታ፣ ፋኖ እንዲፈታ ተወሰኖ፣ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲያልፍ መከላከያው በአማራው ህዝብ ላይ ዘመተበት። ፋኖም ራሱንና ህዝቡን በመከላከል አጸፋውን መለሰ፣ አመፀ። ሂደቱም፣ የራሱን ፈለግ ተከትሎ መጠነ-ሰፊ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ይህን ኢፍትሐዊ ጦርነት ለመመከት የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወሎና የሸዋ ፋኖዎች ማዕከላዊ ዕዝ በመመስረት በጥናትና በዕቅድ እየተመሩ እናም እየተናበቡ ራሳቸውን መከላከል ጀመሩ። ውጊያውም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ቀልብ ሳበ። የዓለም ሚዲያዎችንና የውጭ መንግሥታትን አስተውሎ አገኙ። በአንፃሩ፣ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ከባድ መሣሪያና ድሮን እየተጠቀመ ሴት፣ ወንድ፣ ሕፃን ሳይለይ ጭፍጨፋውን ያካሂዳል። በያዛቸው ከተሞች የሚያገኛቸውን ወጣቶች እየሰበሰበ የደርግን የቀይ ሽብር ዘመቻ በመሰለ መንገድ ያለርህራሄ ግድያ ይፈፅማል። በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን፣ 15 ዓመት ያልሞላቸው ታዳጊዎችን ጭምር፣ እየሰበሰበ ናዚ ጀርመን የተጠቀመባቸውን የከምችት ካምፖች በሚመስሉ ማጎሪያዎች ውስጥ እያሠረ ያሰቃያቸዋል። ይህን የጦርነት ወንጀል የሚያስረዱ ዘገባዎች ከቪዲዮና የዓይን ምስክሮች ትርክት ጋር እየወጡ ስለሆነ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በአዘጋጀው መድረክ ላይ የኢትዮጵያን መንግሥት በጦርነትና በስብዕና ላይ በተፈፀመ ወንጀል (Crime Against Humanity) አጋልጠዋል፣ የበለጠ ክትትልና ምርምር እንዲካሄድም እየሞገቱ ናቸው።

## አካታች ሥርዓት ለመገንባት ዕድሎች ለምን ሊያመልጡ ቻሉ?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ቁልፍ ስፍራ ስላለው የኃይል የፖለቲካ አሰላለፍን (power politics) መፈተሽ ተገቢ ነው። ለጥያቄው መልስ መስጠት ተገቢ የሚሆነው፣ ዛሬ፣ በ2016 ዓም ኢትዮጵያን ሌላ ዕድል ሊገጥማት እንደሚችል ታሪክ እያሳየን ስለሆነ ነው። ከዚህ በፊት እንደሆነው ሁሉ ይህ ዕድል ይመክናል ወይስ ካለፉት ተመክሮዎች በመማር የተሻለ አካሄድ ተከትሎ የተቃና እና የተሳካ ዕድል ሊያስገኝ ይችላል? መፍትሄው እጃችን ላይ ነው።

ለአካታች የሽግግር ሂደት የተፈጠረ ዕድል የሚመክነው አንድም ስልጣን ላይ ያሉ ኃይሎች በያዙት ጦር ለመጠቀም ምንም ዓይነት ችግር የሌለባቸው ሲሆን ነው። በተጨማሪም አካታች የሆነ ሂደትን እንዲከተሉ የሚያስገድዳቸው የተደራጀ ሕዝባዊ ኃይል አልመኖሩ ነው።

በመጀመሪያ ግን የበፊተኞቹ ዕድሎች ለምን እንደመከኑ እንፈትሽ።

### ዋና ዋናዎቹ ሂደቶችን በአጭሩ እንቃኝ

- ከ1953ቱ ኩዴታ ሙከራ በኋላ የአጼ ኃይለ ስላሴ መንግስት፣ መፈንቅለ መንግስቱን የሞከሩ ኃይሎችን አጠፋ። ሌላ ተገዳዳሪ ጉልበት ያለው ሃይል ባላመኖሩ ቀጣዩን ሂደት በተለመደው የብቸኛ መንገድ ቀጠለ።
- በ1966 ዓም ሥልጣን የተረከበው የልጅ እንዳልካቸው መኮንን መንግስትም፣ ከጀርባው የአጼው መንግስት ወታደሮች ስለነበሩ፣ ብቻውን ስልጣን አስጠብቆ መሄድ ይቻላል የሚል ተመሳሳይ ጉዞ ተከትሎ ካዘገመ በኋላ፣ ወታደሩ ሊከዳው እንደሚችል ሲረዳ፣ ወታደሩን የጨመረ አካታች መንግስት ለማቋቋም ሙከራ አደረገ። ግን ዘገየ።
- በ1967 ዓም ስልጣን የያዘው ደርግ፣ በጠመንጃ ኃይል ሁኔታዎችን መቆጣጠር ይቻላል የሚል ንቃተ ህሊና እና ድርጅታዊ ቁመና እስኪላበስ ድረስ አካታች የሽግግር ሂደት ለመከተል የተወሰኑ ምልክቶች አሳየ። ወታደሩን በቁጥጥሩ ስር መዋሉንና ጉልበቱ መፈርጠሙን ካረጋገጠ በኃላ፣ የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከነኑ ማሰለፉን ከተረዳና አቅም ያለው ብቸኛ ማእከል መሆኑን ሲገነዘብ፣ የሲቪል ተገዳዳሪ አካላትን ተራ በተራ አዳከመ፣ መታ። መሳሪያ የያዙ ሃይሎችንም በጠብመንጃ ማጥፋት ይቻላል በሚል እምነት፣ ለአካታችነት በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘጋ።
- በ1968 ዓም በደርግ ውስጥ የተነሳው ልዩነትና ቅራኔ ለሻለቃ መንግስቱ አሳሳቢና አደገኛ ነበር። ሻለቃ መንግሥቱ ካለደርግ ስምምነትና ፈቃድ፣ መሪ የደርግ አባላትንና ሌሎች ግለሰቦችን በማስገደላቸው ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ ስለተፈጠረ፣ ይህን ሁኔታ ማምከን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆነባቸው። በዚህ ጊዜ፣ ሻለቃው የአብዛኛው የደርግ አባላትን ድጋፍ አጥተዋል። አዲስ አበባ ይገኝ የነበረው 4ኛው ክፍለ ጦርንም አይቆጣጠሩም ነበር። ስለዚህ፣ ጥቂት ወታደሮች ይዘው መፈንቅለ መንግስት ማድረግ ነበረባቸው። አደረጉትም። ጠላት የሚሏቸውንም በአንድ ቅጽበት ሲያጠፉ፣ የተቀሩት የደርግ አባላት ሳይወዱ በግድ አጎነበሱላቸው። ይህ አጋጣሚ የሚያስረዳን፣ ለአካታች ሥርዓት መጥፋት የዲሞክራሲ አለመኖርና፣ በተያያዥም የፖለቲካ ምህዳሩ አስቻይ ሆኖ ተገዳዳሪ የፖለቲካ ሃይሎች ሊፈጠሩና ሊጠናከሩ አለመቻላቸውና መፈንቀለ መንግስትን የመሳሰሉ በደባ የሚካሄዱ አሰራሮች ተጨማሪ ችግሮች መሆናቸው ነው።
- ለ17 አመታት ያህል፣ ደርግ፣ ብሔርተኛ አማጽያንን በጉልበት አጠፋለሁ የሚል እምነት አንግቦ በጦርነቱ ቀጠለ። ይሁንና፣ በመውደቂያው አካባቢ ከሻዕብያ እና ከወያኔ ጋር አካታች የሽግግር ሂደት ውስጥ ሊገባ ዳዳው። ረፍዷል።
  ደርግ እንዲወገድ ይፈልጉ የነበሩት የውጭ መንግሥታትም አማጽያኑን ማገዝ ጀምረው ስለነበረ፣ ሙከራውም የትም አልደረሰም።
  በ1983 ዓም ደርግ/ኢሰፓ ተሰናበተ።
- መላ ሀገሪቱን በቁጥጥሩ ስር እስኪያስገባ ድረስ፣ በ1983 ዓም ወያኔ የይስሙላ የአካታች ሂደት ለማስጀመር ሞከረ።ያም ሆኖ ግን፣ ሊገዳደሩ የሚችሉትንና ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ ያላቸው አካላትን ወደ ሽግግሩ ሂደት አልጋበዘም። እንደ ኢህአፓ የመሳሰሉ ተገዳዳሪዎቹን ለማጥፋት ጥረት አደረገ። አዳከማቸውም።፡የኦነግ መሰረታዊ ርእዮት ከወያኔ ጋር ይሰምር ስለነበረ ለተወሰነ ጊዜ ታገሰ። ወያኔ ጉልበቱ መፈርጠሙን ሲረዳ ግን ለኦነግም አልተመለሰም። አባላቱን ገደለ፣ ድርጅቱን አዳከም፣ በመጨረሻ በታተነው።

- የ1997 ዓም ምርጫም አካታች ሂደት የሚሞከርበት ሌላ እድል ነበር። ግልጽነት የተላበሰ ምርጫ እንዲካሄድ ወያኔ ሊፈቅድ የቻለው አሸናፊ ሆኖ እንደሚወጣ፣ (በኢህአዴግ ላይ ህዝቡ የነበረውን ጥላቻ ካለመረዳት) ፣ "እርግጠኛ" የነበረ በመሆኑ ሲሆን፣ ሚያዚያ 30 የተካሄደው እጅግ ግዙፍ ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ አስተያየቱን አስቀየረው፣ ወያኔ ሊሸነፍ እንደሚችል ተረዳ። ከዚያም፣ ምርጫውን አጭበረበረ። በዚያ አላቆመም። ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም ተቃውሞውን አዳከመ። የቅንጅት መሪዎቹን አሰረ። ሰልፈኞችን በተነ።የ ሚገድለውን ገደለ። ኢትዮጵያንም ለ13 አመት ለጨለማ ጊዜ ዳረገ።
- በ2010/11 (ግሪጎሪያን በ2018) ዓም ወያኔን ሊያስወግድ የቻለው የህዝብ ትግል አንድ ታሳቢ ቢሆንም፣ በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው የውስጥ የስልጣን ሽኩቻም ትልቅ ሚና ነበረው። አመጹ እየቀጠለ ሲሄድ፣ ወያኔ እንደቀድሞው መግዛት ተሳነው። ሕዝቡም እንደቀድሞ አልገዛም በማለት በአሻፈረኝነቱ ቀጠለ። ሥርዓቱ ሊፈረካከስ እንደሚችል ሲረዳም፣ ጊዜ ለመግዛት በማሰብ ወያኔ አፈገፈገ። ሥልጣኑንም ለኢህአዴግ 2 ለቀቀ። የስልጣን ሽግግር ተደረገ። ወያኔ የተቀማውን ሥልጣን ለማስመለስ ጦርነት ከፍቶ ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመታት ያህል ደማች።
- የበላይነት በመቀዳጀቱ የተኩራራው የብልጽግና መንግስት በ2015 ዓም 40 ሚልዮን በሚገመት የአማራ ተወላጆች ላይ ጦርነት ከፈተ። በተለመደው መንገድም የአማራውን እምቢተኛነት በነፍጥ ለመደምሰስ ወሰነ።

እንደማናቸውም አምባገነናዊ መንግሥቶች ሁሉ የብልጽግናውም ወደ ድርድር ሊገባ የሚችለው ለሥልጣኑ አስጊና ተገዳዳሪ የሆኑ ድርጅቶች (የፖለቲካ ሃይሎች) ሲኖሩ ብቻ ነው። ተገዳዳሪነት የሚለካው በወታደራዊ ቁመና እና ኃይል ብቻ ሳይሆን፣ በህዝባዊ ቅቡልነት፣ በፖለቲካ ብስለት፣ በአስተዳደር እውቀትና በመሳሰሉት ጭምር ነው። በተጨማሪ፣ እንደ ፋኖ ያሉ ህዝባዊ ሀይሎች፣ ከአካባቢያቸው ባለፈ በሌላ ክልሎች የሚገኙ ዜጎችን ከጎናቸው ማሰለፍና የፖለቲካ ሂደቱ አካል ሲያደርጉ ነው የብልጽግናን አገዛዝ ማስጨነቅና ማስገደድ የሚችሉት።
ኢትዮጵያ ከ60 አመት በላይ ለችግር የተዳረገችው የአካታች ሥርዓት ሊፈጠር አለመቻሉ አንዱና ዋናው ምክንያት ነው።

**የአካታች ሥርዓት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች**

- የፈለገውን የሚያደርግ፣ ሲፈልገው በህዝብ ላይ ጦርነት የሚያውጅና የሚከፍት መንግስትና ሥርዓት ተወግዶና አክትሞ ተጠያቂ የሆነ መንግስትና ሥርዓት ይቋቋማል፣
- ህዝብ፣ ሕይወቱን በተመለከተ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ማድረግ፣ ድምፁ እንዲሰማ፣ በምስለኔዎችና በካድሬዎች አስተዳደር ሥር እንዳይሆን ይደረጋል፣
- ሥርዓቱ የህዝቡ አገልጋይ እንጂ ህዝቡ የሥርዓቱ አገልጋይ አይሆንም፣
- ኢትዮጵያ፣ ራቁቷን ያስቀሯት ሌቦች የማይቀራመቷትና የማይቆጣጠሯት አገር እንድትሆን ሁነኛ ሥርዓት ይዘረጋል፣
- መሬት የሌቦች ሲሳይ በመሆን ፈንታ፣ በህዝብ ተሳታፊነት ጭምር የሚነደፍ የመሬት ስሪትና የባለቤትነት ህግጋት ይቀረፃሉ፣
- ለባለሀብት ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቅድሚያን ሰጥቶ፣ የውጭ ዜጎችን የመዋዕለ ነዋይ ፈሰሳ (investment policy) የሚያበረታታ ፖለሲ ተነድፎ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፣
- ስራ አጥነትን ለመከላከል የሚረዱ ፖለሲዎችና አሰራሮች ተነድፈው ስራ ላይ ይውላሉ፣
- ሀገር እንድትበለጽግ፣ ከቢሮክራሲያዊ ማነቆና ከብልሹ አሰራር የፀዳ የአስተዳደርና የንግድ ፖሊሲ ይነደፋል፣
- የትምህርት ፖሊሲ አብዛኛውን ህዝብ ሊጠቀም በሚችል ሁኔታ ይቀረፃል፣
- ከኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የጠፋው ሰላም በዘላቂነት እንዲሰፍን ይደረጋል፣
- የፍትህ ሥርዓቱ የህግ የበላይነት ላይ በተመሠረተ የዳኝነት ሥር ዓት መዘርጋት ላይ ተመስርቶ የህግ ዕውቀት፣ ሙያና ሥነ ምግባር ባላቸው ብቁ ዜጎች እጅ እንዲያዝ ይደረጋል፣
- የመንግስት ዋና ዋና የኃላፊነት ቦታዎች ችሎታ ባለቸው ባለሙያዎች (technocrats) እንጂ በካድሬዎች አይመሩም፣
- የዜጎችን የመንቀሳቀስና መኖሪያ ሥፍራን የመምረጥ መብት የሚያስከብር መንግሥታዊ ሥርዓትና ህግ ይኖራል፣
- የዜጎችን ህይወት መጠበቅና ማስጠበቅ ቅድሚያ ተግባሩ የሆነ መንግስታዊ ሥርዓት ተመስርቶ፣ ዜጎች በጠራራ ፀሀይ ታግተው ለግድያ ዝርፊያና ለሌብነት የሚዳረጉበት ሁኔታን የሚያስወግድ ፖሊሲና አሰራር ይነደፋል፣

- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገበት አካባቢ ሄዶ የመኖር፣ የመስራት፣ ንብረት የማፍራት መብቱ በህግ ይከበራል፣ በሥራ ላይም ይውላል።
- በማንነት ላይ የተመሠረተ ፖለቲካን የሥርዓት መመሪያ ማድረግ በህግ ይታገዳል። የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘርና በሃይማኖት ላይ ተመሥርተው እንዳይቋቋሙ ይደረጋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች መስፈርቶች በርዕዮተ ዓለማዊ፣ በፖለቲካና በሌሎች ጥያቄዎች ዙሪያ ብቻ ይሆናሉ፣
- "ክልሎች" የሚባሉት፣ የአስተዳደር ክፍሎች፣ በዘርና በቋንቋ የሚመሠረቱ ሳይሆኑ፣ ለአስተዳደር፣ ለእድገት፣ ለኢኮኖሚያዊ ግኑኙነት አመቺ በሆኑ ጂኦግራፊያዊ መንገዶች እንዲዋቀሩ ይደረጋል፣
- የህዝቡ መሰረታዊ መብቶች ይከበራሉ፣
- የውጭ ኃይሎችን ጣልቃ ገብነት ይወገዳል፣
- ከባድ ወንጀል የሰሩ ለፍርድ ሂደት ይቀርባሉ፣
- በመላ ሀገሪቱ የእርቀ ሰላም ሂደት ይከናወናል፣

**ዛሬ፣ በብልጽግና ዘመነ መንግስት ያለው ሁኔታ**

በብልጽግና ዘመን አካታች ሥርዓት ሊነግስ ካለመቻሉ ሌላ፣ ኢትዮጵያ እጅግ ግዙፍ የሆነ ችግር እየገጠማት ትገኛለች። ዋነኛው ጦርነት ሲሆን፣ በአማራ ክልል ከፋኖ ጋር በሚካሄደው ጦርነት በርካታ የመከላከያ አባላት ተማርከዋል፣ ተገድለዋል፣ ከእነ ትጥቃቸው ከጦር አውድማዎች ሸሽተዋል። ትክክለኛው አሃዝ ባይታወቅም፣ በተለያዩ የአማራ ክልል በሚደረጉ ውጊያዎች፣ የአገር መከላከያ ኃይሉ በመቶ ሺህዎችና ከዚያ በላይ የሚቆጠሩ አባላቱን አጥቷል። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ኢትዮጵያ ከውጭ የሚደርስባትን ወታደራዊ ጥቃት መመከት አቅቷት ትጠቃለች። ሁኔታውን የከፋ የሚያደርገው በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የታጠቁ ኃይሎች አደረጃጀት፣ ይዘት፣ አስተሳሰብና አሰላለፍ በርካታ ችግሮችን ያዘለ መሆኑ ነው። እናብራራ።

መከላከያው ከሚያዘውና ከሚቆጣጠረው ውጭ 8 ግዙፍና አነስተኛ የሆኑ ተዋጊ ኃይሎች ተፈጥረዋል። እነሱም፣

- በኦሮምያ ክልል ስር የሚገኘው፣ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች ያሰለፈውና በደንብ የታጠቀው የክልሉ ልዩ ኃይል፣
- በቁጥሩ በርካታ ሺህዎችን ያቀፈው፣ በትጥቁም የተጎላበተውና ከአዲስ አበባ ጥቂት ኪሎሜትሮች ርቀት ላይ የሚገኙ አካባቢዎች ውስጥ ዘልቆ በመግባት ጭምር ወታደራዊ እርምጃዎችን የሚወስደው፣ በኦሮሞ ብሄረተኛ ኃይሎች የሚመራው ራሱን "የኦሮሞ ነፃ አውጭ ሃይል" ብሎ የሚጠራው፣
- በትግራይ በተቀሰቀሰው ጦርነት ለሁለት አመት ያህል ሲዋጋ የቆየው፣ በብዙ መቶ ሺህ የሚገመተውና ጥሩ ትጥቃዊ ቁመና ያለው በህወሓት ሥር ያለው ሠራዊት፣
- በመላ የአማራ ክልል እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው፣ አስተማማኝ በሆነ ደረጃ ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው በቅርቡ ደግሞ ትጥቁንና አደረጃጀቱንም እያሻሻለ የሚገኘው የፋኖ ተዋጊ ኃይል፣
- በ2013 ዓም በተቀሰቀሰው የኢትዮጵያ ህልውና ጦርነት አንቱ የተባለ ሀገር-አድን የሆነ ተግባር ያከናወነውና በአፋር ክልል ተደራጅቶ የሚንቀሳቀሰው የክልሉ ልዩ ኃይል፣
- ብዛቱንና ትጥቃዊ ቁመናውን በትክክል ለመናገር የማይቻለው የወልቃይት-ጠገዴ አማራዊ ማንነትን ለማስከበር የተደራጀው በበርካታ ሺዎች የሚገመተው ታጣቂ ኃይል፣
- ጥሩ የውጊያ ተመክሮ ያለው፣ የሶማሌ ክልል ልዩ ሃይል፣
- በየክልሉ የሚንቀሳቀሱ (በሲዳማ፣ በቀሪው ደቡብ፣ በጋምቤል፣ በቤነሻንጉል) ቁጥራቸው የማይታወቅ ታጣቂ ኃይሎች ናቸው።

በሀገሪቱ ከበድ ያለ ተጽእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉት ሶስቱ የታጠቁ ሀይሎች ማለትም የኦሮሞ፤ የአማራና የትግራይ ሀይሎች መሀል ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳለ ባይታወቅም በኦነግና በህወሃት መሀል ግንኙነት እንዳለ አንዳንድ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። ሆኖም፣ ሁሉም በሚባል ደረጃ ከብልጽግና መንግስት ጋር የቀረበ ግንኙነት አላቸው ብሎ መናገር ይከብዳል። ህዋሀት ከብልጽግና ጋር ገብቶ ከነበረበት ጦርነት ገና ትናንት

ነው የወጣው። ፋኖ እና ኦነግም (ኦነግ ሸኔ) ዛሬም ጦርነት ላይ ናቸው። የሶማሌ ክልላዊ ሃይልና የአፋር ክልላዊ ሃይልም፣በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ጠንካራ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ወታደራዊ ኃይሎች በተጨማሪ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ቁርኝት (ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጂኦ-ስታራቴጂያዊ) ሙሉ በሙሉ ያልተበጠሰ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ ሰላም ካጣች ኤርትራንም ሊያውክ ስለሚችል፣ ያን መሰል ሁኔታ ቢፈጠር የኤርትራ ወታደራዊ ኃይል በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ እጁን ሊያስገባና ጥቅሙን ለማስከበር እንደሚሞክር ከህወሃት ጋር ከተደረገው ጦርነት ወቅት መረዳት ይቻላል። በእርግጥ፣ በቅርቡ ከኤርትራ እንደሚሰማው መንግስቱ ወታደራዊ ዝግጅት በማድረግ ላይ ነው። በርካታ ወጣቶችም ስልጠና እንዲወስዱ እየተገደዱ ናቸው።

**በሀገሪቱ የታጠቁ ኃይሎች**

የመከላከያ ኃይሉን በሙተው ከላይ የተጠቀሱት 8ቱ የታጠቁ ኃይሎች ቁጥር ቢደመር፣ በአነስተኛ ግምት 1 ሚሊዮን ሊደርስ ይችላል። እነዚህ የታጠቁ ኃይሎች፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እጅግ ዘመናዊ የነብስ ወከፍ መሳሪያዎች ባለቤቶች ናቸው።አባሎቻቸውም በቂ ወታደራዊ ሥልጠና የወሰዱና ልምድ ያካበቱ ከመሆናቸው ባሻገር፣ በችግር ተፈትነዋል። አንዳንዶቹ ከቡድን መሳሪያ በላይ ያላቸው ሲሆኑ፣ በተግባር አውለውታል፣ እያዋሉትም ናቸው። በንጽጽር፣ የመከላከያ ኃይሉን ትክክለኛ ቁጥር መናገር ባይቻልም፣ ሁሉም ዘርፎች ተደምረው ከ500ሺህ ሊበልጡ አይችሉም። እናም፣ በተለያየ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሰማሩ ሁሉም ወይም ከፊሉ እንኳን የታጠቁ ኃይሎች በሀገር መከላከያው ላይ የተቀናጀ ውጊያ ቢከፍቱ መከላከያው ሁኔታውን ሊቋቋም አይችልም። በጥቂት ወራት ውስጥ ይዳከማል።

ዛሬ ላይ መከላከያው አሁን የደረሰበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሊወድቅ የቻለው አንዱና ዋነኛ ምክንያት በሀገራችን ውስጥ አካታች ሥርዓት ሊፈጠር ባለመቻሉ መሆኑን ከላይ አሳይተናል። ከዚያ ባልተናነሰ ሁኔታ ደግሞ፣ ሌሎች ተጓዳኝና ተዛማጅ ሁኔታዎችን እንቃኝ።

በኦሮሚያ ክልል በብልፅግና ፓርቲ ውስጥ የተሰገሰጉ ግለሰቦች ተራው የእኛ ነው በሚል አስተሳሰብና ትዕቢት የወሰን መስፋፋት አባዜ ውስጥ ገብተው፣ ከሲዳሞ፣ ከሱማሌ፣ ከጋምቤላ፣ ከቤንሻንጉል፣ ከአፋር ክልሎችና ከጉራጌ ብሔረሰብ፣ ከጉጂዎች፣ ከጋሞዎች፣ ወዘተ ጋር እየተራኮቱ ናቸው። ከሱማሌ ጋር እስከመታኮስ ደርሰዋል። አፋርና ኢሳዎችን በማጋጨት ጭምር የወሰን ጉዳይ በየጊዜው ይነሳል።

እነዚህ በተለያየ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሰማሩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የብልጽግና (የኢህአዴግ) ካድሬዎች በህዝቡ ላይ በየቀኑ የሚያደርሱት ግፍና ብልግና ሳያንስ፣ እነርሱን መቆጣጠር አለመቻሉ የህዝቡ ብሶት እየጨመረ መሄድ ብቻ ሳይሆን፣ በብልጽግና እና በፊተኛው ሥርዓት መሀል ያለውን ልዩነት ማየት እንኳን አሰቸጋሪ ሆኗል። በአብይና በፓርቲው ላይ ህዝቡ ያለው አመኔታና ድጋፍም እየተመናመነ ሄዷል። አብይ እንደመሪ፣ ብልጽግናም እንደ ገዢ ፓርቲ ሀገሪቷ ያለችበትን ዘርፈ ብዙ ችግር የመፍታት አቅማቸውና ተነሳሺነታቸው ከባድ ጥያቄ ውስጥ ወድቋል።

ጋዜጠኞች ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት ሙያቸውን እንዳያከናውኑ፣ የፖለቲካ ተሚጋቾች በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ፣ እንዳይናገሩ ተደርጎ ያለፍርድ ሂደት በነሲብ ለእሥር ይዳረጋሉ። ድብደባና ሰቆቃ ይደርስባቸዋል። በዋስ እንዲለቀቁ የተበየነላቸው ተከሳሾች በፖሊስ ታፍነው እንደገና ይታሰራሉ። ከፖሊስና የደህንነት መዋቅር ውጭ እንደናዚዎች ጌስታፖ (Gestapo) የተደራጁ ቡድኖችን፣ የምክር ቤት አባላትን፣ ተቃዋሚዎችን፣ የፖለቲካ ተሚጋች ጋዜጠኞችንና ሌሎችን ከየቀያቸው፣ ከየአደባባዩ አፍነውና ጠልፈው በመውሰድ ቀጥቅጠውና አካል ጉዳት አድረሰውባቸው በየመንገዱና በየጥሻው ወርውረዋቸው ይሄዳሉ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገንዘባቸውን ከፍለው የሚዘጋጁት ጉባዔና የሚጠሩት ስብሰባ በመንግሥት ቀጥተኛም ሆነ ስውር ትዕዛዝ ይታገድባቸዋል።

በጠቅላይ ሚንስትር ዓብይ የሚመራው የብልጽግና መንግስት፣ ለዜጎች ፍትህን፣ እኩልነትን፣ ሰላምና የኑሮ መረጋጋትን ሊያመጣ አልቻለም። ከሁለት አመት በፊት የተካሄደው አውዳሚ ጦርነትም ኢትዮጵያን እጅጉን ደቁሷታል። የሀገርና የዜጎች ቁስል ገና ባለመሻሩ፣ ኢትዮጵያ በታሪኳ ገጥሟት የማታውቀው ዓይነት ፈተና ውስጥ ወድቃለች።

በጸጥታ መናጋትና በእርሻ ግብዓቶች እጦት በከፍተኛ አምራች አካባቢዎች የእርሻና የመዝሪያ ወቅቶች በመባከናቸው፣ በሚቀጥለው አመት የምርት እጥረት ያለጥርጥር ይኖራል። ስለሆነም፣ እያሻቀበ ከሚሄደው የኑሮ ውድነትና ከእህል አቅርቦት መጥፋት ጋር በተያያዘ ምክንያት ሀገሪቱ ከፍተኛ ችግር ይገጥማታል። ይህን መሰሉ ሁኔታ በንጉሱ፣ በደርግና በህወሃት ዘመን ታይቶ የነበረ ቢሆንም፣ የመጪው ዘመን ችግር

ከፊተኞቹ የሚለየው ጥቂት ክፍለ ሀገሮችን ወይም አካባቢዎችን ብቻ ሳይሆን መላ ሀገሪቱን ሊያዳርስ መቻሉ ነው። እንደ ዓለም ባንክ፣ የአሜሪካን የተራዶኦ ድርጅትና ሌሎች ታዛቢዎች ከሆነ፣ ከ30 ሚሊዮን በላይ ርሃብተኛ፤ ከአምስት ሚሊየን በላይ የተፈናቀለ ሕዝብ ያለባት አገር ሆናለች። የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ሌላው ቀርቶ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ወገኖቻችንን ከፉኛ ጎድቷቸዋል።

በመንግስትና በተለያዩ የታጠቁ ኃይሎች መሀል በመካሄድ ላይ የሚገኘው ጦርነት በምን መልክ ሊቋጭ እንደሚችል መተንበይ ባይቻልም፣ ሀገሪቱ በቀጣይ ትደማለች፣ ወገን ያልቃል፣ ኢኮኖሚው ይበልጥ ይዳሽቃል። ሰላማዊ የትግል ዘዴ አክትሞለት ውርርዱ በነፍጥ ብቻ ይሆናል። መንግስቱ የብሔርተኛ አጀንዳ አስተናጋጅ እንደመሆኑ፣ የዘር ጥላቻው እየከረረ ሄዶ ሀገሪቱን ለከፋ ሁኔታ ሊዳርጋት ይችላል።

በየክልሎቹ በሚነሳው ችግርና ሁከት ምክንያት፣ ከ1761-1847 ዓም ድረስ እንደዘለቀው እንደ ዘመነ መሳፍንቱ ጊዜ አካባቢዎችን ማስተዳደር ያዳግታል። ዛሬ በአማራ ክልል እንደሆነው፣ በሌሎች ክልሎችም መንግስቶቹ ሊፈራርሱ ይችላሉ። ዛሬ በአማራ ክልል እንደታየው፣ ክልሎች ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎች ታጣቂ ኃይሎች ስር ይወድቃሉ።

እስከ ዛሬ በሚስተዋለው፣ የወልቃይት፣ የጠለምትና የራያ ሕዝብ ጥያቄ የብልጽግና መንግሥት በሚከተለው አካሄድ ፍትሃዊ የሆነ መፍትሄ ሊያገኝ የሚችልበት ዕድል እጅግ ጠባብ ነው። ፌዴራል መንግሥቱ አሁን የጀመረውን አማራውን በጦርነት ለማንበርከክና ከፋኖና ከህዝቡ ጋር የሚያደርገው ጦርነትን በያዘው መንገድ ከቀጠለ በጭራሽ አይበርድም። ይህም በእሳት ላይ እንደሚርከፈከፍ ቤኒዚን ከአማራው ክልል አልፎ ሀገራዊ ችግሩን ያወሳስባል እንጂ መፍትሄ አያመጣም። እናም ምን ሊከተል እንደሚችል እንመልከት።

**ሊሆን ከቻለ 1** (Scenario 1) - **በመከላከያውና በፋኖ መሀከል የሚደረገው ጦርነት ከቀጠለ**

ጦርነቱ ሊቀጥል የሚችለው፣ በዋናነት ስልጣን ላይ ያለው መንግስት በተለያዩ ምክንያቶች ለመደራደር ዝግጁ ሳይሆን ከቀረ ሲሆን፣ ሰላማዊ የሆነው መንገድ ሁሉ ተዘግቶ ችግሮችን በጦርነት ብቻ ለመፍታት የሚደረገው ሙከራ ይቀጥላል። በፋኖ እና በመከላከያው መሀል የተነሳውን ጦርነት የሚያወሳስበው፣ አማራው ከከፍተኛ ትዕግስት በኋላ ህልውናውን ለማስከበር የሚያደርገው የመከላከል ጦርነት በመሆኑና ሽንፈት ማለት ለአማራው እንደ ሕዝብ መጥፋት ወይንም የበታች ተደርጎ መገዛት በመሆኑ ነው። ስለሆነም፣ አማራውም ሆነ በእሱ ስም በፊታውራሪነት ጦርነቱን የሚመራው ፋኖ ሽንፈት ምርጫቸው አይሆንም። የቪየትናም ሕዝብ ከግዙፉ የአሜሪካ ጦር ጋር ለብዙ አመታት እንደታገለው ሁሉ አማራው ያን አማራጭ ይወስዳል።ፋኖን ይደግፋል፣ ይደብቃል፣ ተዋጊ ይሰጣል፣ በውጊያ፣ በስንቅና በሚችለው ሁሉ ይተባበራል። በአጭሩ፣ ጥቂት መቶ ሺህ የመከላከያ ሀይል ከሰላሳና ከአርባ ሚልዮን ሕዝብ ጋር ይገጥማል።

ይህ ሂደት በአጠቃላይ በኢትዮጵያ፣ በተለይም በአማራው ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ ወዘተ፣ ችግር ይፈጥራል። ለብዙ አመታት ሲገነቡ የነበሩ ተቋማት፣ እስከዛሬ ያልፈረሱትም ይፈራርሳሉ። ጦርነቱ እየተራዘመ በሄደ ቁጥር በሀገር ደረጃም ሆነ በክልል የቀውሱ መጠን እየሰፋ ይሄድና ሀገሪቱ የብዙ አመታት የኋልዮሽ ጉዞ ታደርጋለችል። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ አማራውም እንደ ክልል እጅግ ከባድ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ። ጦርነቱ በቀጠለ መጠን፣ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚለቀቀው በጀት ይቆምና፣ የአማራ ክልልና ሌሎችም ፈተና ውስጥ ይወድቃሉ። በሌላ በኩል፣ ጦርነቱ የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብት እየቀረጠፈ ሲሄድ፣ ፌደራል መንግስቱ ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ውስጥ ይወድቃል። ከአማራው ክልል ከታክስና ከመሳሰለው የሚገባው ገቢ ስለሚቋረጥ በሀገር ደረጃ ከፍተኛ የበጀት እጥረት ገጥሞት፣ ፌደራሉ መንግስቱ ሀገራዊ በጀቱን መሸፈን ያዳግተዋል። አገሪቷ ለጦር ኢኮኖሚ (war economy) በመዳረጓ፤ ኢኮኖሚውም ይበልጥ እየተሽመደመደ ይሄዳል። ንግድ ይዳከማል። ስራ አጥነቱ እየሰፋ፣ ድህነቱም ስር እየሰደደ ይሄዳል። ሙስናው ጣሪያ ይነካል፣ የሀገሪቱ ኢኮኖሚም በባሰ ደረጃ ያዳሽቃል፣ ሰላም ይጠፋል። መከላከያው እየተዳከመ በሄደ ልክ፣ በኢትዮጵያ ምድር የሚገኙትና እስከ አፍንጫቸው የታጠቁት በርካታ ኃይሎች ትንቅንቅ ውስጥ እንዲገቡ ዕድል ይከፈታል።

ኢትዮጵያ በየክልሉ በሚገኙ የጦር አበጋዞች (war lords) ስር ትወድቃለች። እነሱም የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ የማያባራ ውጊያ ውስጥ ይጠመዳሉ። ሀገሪቱ በደም ጅረት ትሸፈናለች። ረሀብና ችጋር የበለጠ ይስፋፋል። ለእርስ በእርስ ውጊያና የዘር ፍጅት መደላድሉ ይመቻቻል። የሕዝብ ዕልቂት ይደርሳል፣ በተለይ አዛውንቶች፣ አሮጊቶች፣ ሴቶችና ህፃናት ላይ ችግሩ፣ እጦቱ፣ጉዳቱና ሞቱ ይበራከታል። በህክምና እጦት ብዙ ሰው ይሞታል፣ ይጎዳል። ትምህርት መስጠት ይስተጓጎላል፣ ተተኪ ትውልድ ይመክናል። አብዛኛዎቹ ለሥነ ልቦና ቀውስና ለአዕምሮ በሽተኛነት ይዳረጋሉ።በእብሪተኛነትና በጎጠኛነት የሰላሙን ጎዳና ላለመቀበል ወስኖ የዕልቂት ጎዳና የመረጠው የፌደራል መንግስትና የቀድሞው ኦህዴድ የዛሬው ብልጽግና፣ የመከላከያውና የኦሮሞ ልዩ ኃይሉ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዓብይና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት፣ አቶ ሽመልሽ አብዲሳ ሁለት ሁኔታዎች ይገጥሚቸዋል። የመጀመሪያው ሁኔታ አሁን የምናወሳው የሊሆን ከቻለ 1 (Scenario 1) አካል ነው። (ሁለተኛውን በሊሆን ከቻለ 2 (Scenario 2) ላይ ይመልከቱ) ።

ጠቅላይ ሚኒስቴሩና ተባባሪያቸው የኦህዴዱ መሪ እንደጋዳፊና ልጆቹ ወደ ታሪክ ዘብጥያ ይወርዳሉ። ኢትዮጵያ እንደ አገር ትጠፋለች፣ (failed state) ትሆናለች። ታሪካዊ ጠላቶቿ ሰላም በማስከበር ስም ይከፋፍሏታል፣ ሊከፋፈሏትም ይችላሉ፣ ከዚህ ማናችንም አናተርፍም። ኢትዮጵያ፣ እንደእነ ሊቢያና የመን፣ የመሳሪያ ልውውጥ የሚካሄድባት የንግድ ማዕከልና ለቅጥረኛ ወታደሮች መፈልፈያነት ትዳረጋለች። አሸባሪዎች ከውጪና ከአገር ውስጥ የሚቆጣጠሯት ትሆናለች።

የ120 ሚሊዮን ህዝብ ሀገር ከሆነችው ኢትዮጵያ በመነሳት፣ ስደተኞች አውሮፓን፣ ሌሎች የአፍሪቃ ሀገራትንና መካከለኛው ምስራቅን ያጥለቀልቃሉ። አካባቢው የቀውስ ቀጠና ይሆናል። በዐባይ ግድብ መሰራት የተከፉ ሀገራት ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ኢትዮጵያን ከስከ አሁን ከጎዷት በበለጠ ለመጉዳት ይነሳሉ። የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ተባባሪዎችንም ያገኛሉ። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሀገራዊ መንግስት መዳከምና መዛል በኢትዮጵያ ውስጥ ለሥርዓት አልበኝነት መፈጠር፣ ለጂሃዲስቶችና አልሸባብን ለመሳሰሉ ቡድኖች ዓላማ መሳካት ትልቅ አጋጣሚ ይሆናል።

በተለይም የሀገር መከላከያው ሠራዊት በአማራ ፋኖ፤ በኦሮሞ ነፃ አውጭ ሠራዊት፣ አድብቶ በሚመታ ህወሓት ጭምርና በሌሎች ታጣቂ ሀይሎች (የቅማንት፤ ጉምዝ፤ የጋምቤላ፤ ወ.ዘ.ተ.) እየደረሰበት ባለው ጥቃት የመዳከም ብቻ ሣይሆን የመፈራረስ አደጋ ሊገጠመው ይችላል። የዓቢይ አምባገነን መንግሥት የአማራ ክልል ልዩ ሀይልን የመበተንና የፋኖን ትጥቅ የማስፈታት አዋጅ ተከትሎ በተፈጠረው ችግር ምክንያት የአማራ ተወላጆችና የሌሎች ብሄረሰብ ተወላጆችም የመከላከያ ሠራዊትን እየለቀቁ ፋኖን ተቀላቅለዋል። የሃገሪቱ ችግር እየተባባሰ በሄደ ቁጥር በኦነግ ሠራዊትና በሌሎችም ታጣቂዎች በኩል ተመሣሣይ ክስተት እንደሚፈጠር መገመት ይቻላል። ውሎ አድሮ፣ በየክልሉ የተመሠረቱት ልዩ ሀይሎች በሰው ሀይል፤ በመሣሪያ ብዛትና ጥራት እንዲሁም አደረጃጀት በመጠናከር መከላከያ ሠራዊቱን የሚገዳደሩ ብቻ ሣይሆን ጭራሽ እንዳልነበር ሊያደርጉት ይችላሉ። ዩጎዝላቪያ መፍረስ የጀመረችው የሀገሪቱ መሪዎች የአንዷን ሪፓብሊክ ልዩ ሀይል እንዲፈርስና መሣሪያውን እንዲያስረክብ ባዘዙ ጊዜ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ሊሆን ይችላል ተብሎ ከሚገመቱት መሀል አንዱ ሲሆን፣ ጉዳዩ ወደ ሌላም ምልከታ ይወስደናል። የፌደራል መንግስቱም ሆነ መከላከያው ቢዳከምና ቢጠፉም ብሔርተኛው የኦሮሙማ ኃይል ከመጥፋት ተርፎ ፋኖን አጠፋ ብለን እንገምት።

ይህ ሁኔታም ወደሚቀጥለው ሊሆን ከቻለ (Scenario) ይወስደናል።

### ሊሆን ከቻለ 2 (Scenario 2) - ብሔርተኛ ኃይሎች በማበር ፋኖን አዳክመው የበላይነት ከተቀዳጁ

ጥቂት የኦሮሞ፣ የትግራይና የሌላ አካባቢ ብሔርተኛ ኃይሎች በጋራ በማበር ፋኖን አዳክመው የበላይነት ተቀዳጁ እንበል። ይህ ሁኔታም፣ በአንድ በኩል እነዚህ ጥቂት ብሄረተኞች፣ ለረዥም ዘመን ሲያቅዷቸው የነበሩ ውጥኖቻቸውን ስራ ላይ ለማዋል ጥርጊያውን ያመቻቻል፣ ለኢትየጵያም የሲኦል በር ብርግድ ብሎ ይከፈታል።

የኢትዮጵያዊነት እምነት፣ በአግላይና በከፋፋይ ብሔርተኝነት ይተካል። የርስ በርስ ጥላቻም እጅጉን ይጠናከራል። የኢትዮጵያ ስም ጭምር ሊለወጥ ይችላል። ኢትዮጵያ ታሪክ ትሆናለች። የሶስት ሺ (3, 000) ዓመት ሥልጣኔ ደብዛው እንዲጠፋ ይደረጋል። ታሪኳም በአዲስ መልክ ይፃፋል፣ ይከለሳል። በባህሉ፣ በንግዱ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው፣ በጥቅሉ በሁሉም ዘርፎች የበላይ በሆኑት ጥቂት ብሔርተኞች በሚያራምዱት እምነት ይተካል። ብሔርተኝነት ከነክልልተኛነቱ ይነግሳል። በኢህአዴግ ቀዳማዊ/በህወሃት ዘመን ተባባሪ የነበረው ተረኛው የብልጽግና ገገር አካል የሀገሪቱን ሀብት እንደፈለገው ያደርጋል፣ ይዘርፋል። ሁሉንም ነገር የእኛ እናድርግ ባይነትና ሌሎች ኢትዮጵያውያንን የማግለል፣ የርስበርስ ጥላቻንም የማስፋፋት ጅምር ሥራዎች ይቀጥላሉ። ሁኔታውም፣ ወደእርስ በእርስ ፍጅት (ጄኖሳይድ) ጥንስስ ሊወስድ ይችላል። ከዚያም፣ መረጋጋትና ሠላም፣ ሀገራዊ ልማትና ዕድገት የወሀ ሽታ ሆነው ይቀራሉ።

ፋኖን ያሸነፈው ይሄ ኃይል ተቀናቃኝ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ብሔረተኛ ኃይሎችን በቁጥጥሩ ስር ማድረግ አያዳግተውም። ጊዜውን ጠብቆም ይሄ የኦሮሞ ገገር አካል የበላይነት እንዲጎናጸፍ ያበቁትን ተባባሪዎቹን፣ እነህወሃትንና ሌሎችን ጭምር ተራ በተራ ቀርጥፎ ይበላል። በርካታ አካባቢዎችንም ይቆጣጠራል።አማራ ክልል በመዝለቅ የምዕራብና የሰሜን ሸዋ አካባቢዎችን፣ ደቡባዊና ሰሜናዊ ወሎን፣ ደቡባዊ ትግራይን፣ በኒሻንጉልን፣ እነ ሃዋሳን፣ ወዘተ፣ አግበስብሶ የኦሮምያ አካል ያደርጋል። በአጭሩ፣ ኦሮምያ በሀገር ውስጥ ሌላ ሀገር ይሆናል።

አማራውም እንደ ሕዝብ መኖር የማይችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። ከ30 እና ከ40 አመት በፊት የተጀመረው ፀረ-አማራ ትርክት ስጋ ለብሶና ነብስ ዘርቶ ሰፊ የስነ ልቦና ጦርነት ይካሄዳል። አማራው ይዋረዳል፣ ለተገዥነትና ለውርደት ኑሮ ይዳረጋል። በቅርቡ አንድ የኦሮሞ ብሄረተኛ ግለሰብ በሶሻል ሚድያ ላይ እንዳለው፣ በየቦታው የኦሮሞ ወታደራዊና የሃይማኖት ተቋማት እንዲሰማሩ ተደርገው፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ነጭ ቅኝ ገዢዎች በአፍሪቃ ምድር የሰሩት ታሪክ ይደገማል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ሃይማኖትና የኢትዮጵያ ነባሩ የሙስሊም ዕምነት ላይ ከፍተኛ ጫናና የመፈራረስ ዕጣ ይገጥማቸዋል። አሁንም ከባድ ጥቃት እያስተናገደች ያለችው ቤተ ክርስትያኗ ከነተቋሞችዋ እንድትዳከምና እንድትሰነጣጠቅ ይደረጋል። ለኢትዮጵያ ነፃነት መጠበቅ ምሰሶ ሆነው የቆዩት የክርስትናና የእስልምና የሃይማኖት ኢትዮጵያን እንደ ሀገር በአንድነት የማቆየትና ህዝቡን የማስተሳሰር ታሪካዊ ሚናቸው ይደበዝዛል። ይህም፣ ከሌሎች ጎጂ ጫናዎች ጋር ተዳምሮ በአዲሱ ትውልድ ላይ የሚያደርሰው የሥነ ልቦና ስብራት ሀገራዊ እሴቶቹን ያጠፉበትና ሀገር ተከላካይ አጥታ በቀላሉ በአክራሪ ብሔርተኞች አገዛዝ ስር ትወድቃለች። አዲስ አበባ ፊንፊኔ ትሆናለች፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማም ይቀየራል። ኦሮሚፋ የሀገሪቱ ዋነኛ ቋንቋ ይሆንና፣ መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወዘተ እንዲጠቀሙበት ይደረጋል።

ሌላ ቦታ እንደተጠቀሰው፣ ለአማራው ሽንፈት ማለት እንደ ሕዝብ ከምድረ-ገጽ መጥፋት በመሆኑ ሌላ አማራጭ ይፈልጋል። ጦርነቱን ከአማራ ክልል ውጭ ማስፋፋት ይጀምራል። ፌደራል መንግስቱም ቢሆን ሰላሳና አርባ ሚሊዮን ሕዝብ ማሸነፍ እንደማይችል ስለሚያውቅ ሌሎች ክልሎችንና ወታደራዊ ተቋማትን የጦርነቱ ተሳታፊ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል። በዚያም አለ በዚህ፣ በብልጽግና ፓርቲ የሚመራው መንግሥትና ደጋፊዎቻቸው የፖለቲካ ችግሮችን በሃይል ለመፍታት ይታትራሉ። ሁሉንም ህዝብ ጨቁኖና አፍኖ፣ ሰጥ-ለጥ አድርጎ ለረጅም ጊዜ ሠፊ ሀገርን መግዛት ከባድ ፈተና ይሆንባቸዋል። ያለጥርጥር ሀገራችን የማያባራ ቀውጢ ሁኔታ ዉስጥ ትወድቃለች። በምሬትና በአልሸነፍ ባይነት ነፍጥ የሚያነሱ ትልልቅም ሆኑ ትንንሽ ቡድኖች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ይበራከታሉ። በህዝቡ ዕምቢተኛነትና የተደራጀ ትግል ከሀገር ውስጥ ተቃውሞ እየበረታባቸው ካልመጣ፣ ከውጭም ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎች በርትተው አስገዳጅ ሁኔታዎች ካልገጠሟቸው ወይም ጫና ካላሳረፉባቸው ለሠላማዊ መፍትሄ ፍለጋ ጆሮ ሰጥተውና እሺ ብለው ላይቀበሉ ይችላሉ። ለተወሰነ ጊዜ ሁኔታው ድፍርስርስ እንዳለ ቢቆይም፣ የገዥዎች እጅ እየዛለ ይመጣል፣ መዳከምና መዝለፍለፍም ሊከተል ይችላል። ሠላማዊውን ጎዳና እንዲከተሉ የሚያስገድዷቸው ተግባሮችና ክስተቶች ዕለት ከዕለት እየተበራከቱ በመሄድ፣ በመረጡት መንገድ መቀጠል አስቸጋሪ ምናልባትም የማይቻል እየሆነባቸው ይሄዳል።

## ሊሆን ከቻለ 3 (Scenario 3) - ብልጽግና ከ40 ሚሊዮን ከሚሆን የአማራ ህዝብ ጋር ጦርነት ከቀጠለ

የብልጽግና መንግስት የመጀመሪያ እርምጃ አፍጦና አግጦ ለሚገዳደረው ከ40 ሚሊዮን በላይ ከሆነ የቆረጠ ህዝብ ጋር መታገል ይሆናል። ይህ ሁኔታም፣ ገዥው መንግሥት የሚተማመንባቸው የመከላከያና የኦሮሚያ ክልል ሠራዊት ጠንካራ ምት እየደረሰባቸው በከፍተኛ ቁጥር በሞት፣ በመቁሰል፣ በመክዳት እጅ በመስጠት ይዳከምና ሞራሉ ሲዳሽቅ ፓርቲው የሰላሙን ጎዳና እንዲፈትሽ ያስገድዳሉ። በብልጽግና ፓርቲ ሚስጢራዊ እገዛ ጭምር የተጠናከረው፣ "ኦነግ-ሸኔ" እያለ መንግሥት የሚጠራው፣ ሆኖም፣ ራሱን የኦሮሞ ነጻ-አውጭ ሠራዊት ብሎ የሚጠራው ኃይል፣ አሁን ላይ አልታዘዝ እያለ ይመስላል። በጊዜ ሂደትም የፈረጠመ-እምቢተኛ ሊሆን ይችላል። ይህም፣ ብልጽግና ሰላማዊውን ድርድር እንዲቀበል የሚገፋ ሌላ ሁለተኛው ክስተት ምክንያት ይሆናል። የኦሮሙማ አራማጅ የሆኑና የብልጽግና ፓርቲን እየመሩ ያሉ ተስፋፊዎች፣ በሶማሌ ክልል ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ወረዳዎችን ወደ ኦሮሚያ ክልል ለማጠቃለል ከጀመሩት ትንኮሳ ጋር ተያይዞ አዲስ የግጭት ቀጠና ተፈጥሯል። እንደ ብአዴን መሪዎች የማያጎነብስና በራሱ የሚተማመን የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት መኖሩ ጉዳዩን የሚያከብደው ከመሆኑ ባሻገር፣ የብልጽግና መንግስት ሌላ የጦር አውድማ በመክፈቱ በመከላከያው ላይ የሚደርሰው ጉዳት ይጨምራል። ይህም፣ ብልጽግናን ወደ ሠላማዊ ድርድር የሚገፉ ሌላ ታሳቢ ምክንያት እንደሆነ መገመት ይቻላል።

ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፣ ከቁጥጥር ውጭ ሊሄዱ የሚችሉ ሌሎች የታጠቁ ሃይሎች በአፋርና በሲዳማ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ የመንግሥት ጠንካራ ክንድ ሲዝልና ሲላላ ሊያፈትልኩና መንግስቱን በነፍጥ ሊገዳደሩ ይችላሉ። ለጎልውናው በጣም የሚጨነቀው ገዥ ሃይልም ይህን ሁኔታ የሚስተው አይሆንም።

የኦሮሞ-ብልጽግና ፓርቲ፣ በተስፋፊነትና አላዋቂነት በሚመስል ተንኮል በደቡብ ኢትዮጵያ የጀመረው ክልሉን የመበተንና በፈለገው መንገድ መልሶ የማዋቀር ተግባር አያሌ ችግሮችን ፈጥሯል። በተለይም የጉራጌና የወላይታ ማህበረሰቦች ጠንካራ ተቃውሞ እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል። በሌሎች የደቡብ ኢትዮጵያ አካላት በነበሩ አካባቢዎችም የተለያዩ ብሶቶችን መነሻ ያደረጉ ተቃውሞዎች ተበራክተዋል።

እየተጋጋመ በመምጣት ላይ ያለውና እንደ ቋያ እሳት ውስጥ ውስጡን እየተቀጣጠለ ያለው ይህ ተቃውሞ ቦግ ብሎና ተቀጣጥሎ ገዥ ፓርቲውን ሊበላ እንደሚችል ይረዳል። እናም፣ አጥፍቶ መጥፋት አማራጭ ሊሆን ስለማይችል ሳይወድ በግድ ይጎናበሳል።

ህወሓት መራሹ ኢሕአዴግም (ቀዳማዊውም) ሆነ ብልጽግና መራሹ ኢሕአዴግ (ዳግማዊው)፣ የምዕራቡ ዓለም ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር እስካሁን አልተለያቸውም። ይህን ያደረጉት በአፍሪካ ቀንድ የአሸባሪዎችን እንቅስቃሴ እንዲገቱላቸውና፣ በአፍሪካም ውስጥ ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ኢትዮጵያ ቁልፍ ሚና ትጫወት ስለነበረ ነው። ዛሬ ብልጽግና መራሹ፣ ዳግማዊው ኢህአዴግ ግን እነዚህ ሚናዎችን ሊጫወት ቀርቶ እራሱን የማያድን አካል ሆኖባቸዋል። ይባስ ብሎም፣ ለአፍሪቃ ቀንድና ለዓለም ደህንነት አስጊና በሶማሌው አልሸባብ ጭምር ሀገሩን እያስደፈረ ያለ አካል ሆኗል። ስለዚህም ዓይናቸው ሌሎች ሃይሎች ላይ ያማተረ ይመስላል። ማስፈራሪያቸውንም በአውሮፓ ኅብረት፣ በአምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ በተመድና በዲፕሎማቶቻቸው በኩል እያሰሙ ናቸው። ይህ ታዲያ፣ "ልመናዬ ይሳካልኛል" በሚል መሪ እጅ ውስጥ ያለን መንግሥት ማስደንገጡ የሚጠበቅ ነው፣ ቢለምንም የማይሰጡት መሆናቸውን ሲገነዘብ መደናገጡ የሚጠበቅ ነውና።

ሌላ ቦታ እንደተጠቀሰው፣ ባልፉት ሦስትና አራት ዐመቶች ውስጥ፣ ከፖለቲካና የጸጥታ ችግሮች በተጨማሪ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ችግሮች እጅጉን ተበራክተዋል። ገዢዎቹ፣ ጉዳዩን ባላየ/ባልሰማ ለማለፍ ቢሞክሩም መራራውን ዕውነት ግን ልባቸው ያውቀዋል። መኖር ያቃተው ህዝብ ሊነሳባቸውና ሊበላቸው እንደሚችል ይገምታሉ።ይህ ከማንም ዕይታ ሊሰወር የማይችል ችግር የወለደው ብሶት የሥላማዊ ድርድር አማራጭን የመዳኛቸው ጠባብ መንገድ መሆኑን፣ ጭጋግ በለበሰ ዐይናቸውም ቢሆን ይታያቸውና ጫና ሊፈጥር እንደሚችል ይረዳሉ።

በእነዚህ በተዘረዘሩ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ጭምር የብልጽግና ፓርቲ በሰላም ድርድሩ ሊሳተፍ የማይፈልግ ከሆነ፣ ጊዜ ይውሰድ እንጅ የማታ ማታ ተሸንፎ ከእነጭራሹ ለድርድር የማይቀርብ ሊሆን ይችላል። ለዘለዓለሙም ይሰናበታል። ወዲያም አለ ወዲህ፣ ጦርነቱ በአማራ ክልል ተወስኖ አይቆይም፤ ሌሎች አካባቢዎችንም ያዳርሳል። እናም ይህ ሁኔታ ወደ ሊሆን ከቻለ 4 ይወስደናል።

## ሊሆን ከቻለ 4 - (Scenario 4) ጦርነቱ በአማራው/በፋኖ እና በመከላከያው መሆኑ ቀርቶ አድማሱ ይሰፋል

በመለስተኛ ደረጃም ቢሆን በኦሮምያ ውስጥ በፌደራል መንግስቱና በኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር መሀል ውጊያዎች ይካሄዳሉ። የፌደራል መንግስቱ ፋኖን ማንበርከክ እንደማይችል ብሄረተኛ ሃይሎቹ እየተረዱ ሲሄዱ፣ ከመንግስት ጋር በጥምረት ለመሰለፍ፣ ፌደራል መንግስቱም ስልጣኑን ለኦሮሞ ብሄረተኛ ሃይሎች ለማጋራት ፈቃደኛነቱን ያሳያል። ብሄረተኛ ኃይሎችን በዙሪያው ለማሰለፍ ሲንደረደር ግን አንድ ታሳቢ ጉዳይ ይኖራል። እሱም፣ መንግስትና ብሄረተኛ ኃይሎች በጋራ መሰለፍ ሲጀምሩ፣ የሀገር መከላከያ ኃይል የነበረው ተቋም፣ ያውም እስከዚያ ከዘለቀ፣ በይዘቱም ሆነ በቅርጹ መሰረታዊ ለውጥ ያደርጋል። የብሄረተኛ ኃይሎቹን ከሚደግፉ የመከላከያ አባላት ውጭ ያሉ ኢትዮጵያን ብለው የተቀላቀሉ የመከላከያው አባላት፣ የተቋሙ አባል ለመሆን ያበቃቸው ምክንያት ተኖ ሲጠፋ፣ ለተወሰኑ ወገኖች ጥቅምና ፍላጎት መሰለፍ ምርጫቸው ስለማይሆን የሀገር መከላከያውን ይለቃሉ። ተቋሙም የሀገር መከላከያ መሆኑ ቀርቶ የጥቂት ብሄረተኛ ቡድኖች ጥቅም አስጠባቂ አካል ይሆናል። ያ ብቻ አይደለም። የሀገር መከላከያ ኃይሉ ይፈራርስና የኢትዮጵያን ዳር ድንበር የሚያስከብር ኃይል ይጠፋል፣ ሀገሪቱም እጅግ ለከፋ ችግር ትጋለጣለች። በሌላ በኩል፣ ፌደራል መንግስቱ፣ ወልቃይት፣ ፀለምትንና ራያን ለህወሃት አሳልፎ ለመስጠት ይሁንታን ሲያሳይ፣ ህወሃትም ሆነ ከትግራይ ክልል የሚነሳው ጦር ከመሰል ብሄረተኛ ኃይሎች ጋር በመተባበር ይዘምታል። የፌደራል መንግስቱ ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ለመፍጠር ሲሞክር፣ በአንፃሩ በአማራው ክልል ውስጥ አዲስና ሌላ የኃይል አሰላለፍ ይፈጠራል። በየክልሉ የኢትዮጵያን መፍረስ የማይፈልጉ ኃይሎች አገሪቱን ለማዳን ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ የትግራይና የኦሮምያ ወገኖችም ጭምር።

ህወሃትን አምርሮ የሚጠላው የኤርትራ መንግስት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጦርነቱ አካል እንዲሆን ሁኔታው ይጋብዘዋል። የኤርትራ መንግስት ይህን መሰሉን እርምጃ የሚወስደው አማራውን ወይም ፋኖን በመደገፍ ብቻ አይደለም። እንዲያውም ዋናው ምክንያት ያ አይደለም። የህወሃት መጠናከርም ሆነ ከበስተኋላው ሆኖ የሚደግፈው የምዕራቡ ኃይል፣ ኤርትራን ሊያዳክም ብሎም ሊያጠፋ ይችላል ብሎ ማሰቡ ነው ዋናው ምክንያት። እንደሚታወቀው፣ ኤርትራ ከሩስያ ጎን በመሰለፍ፣ የቀይ ባህር ላይ የሩስያ የባህር ኃይል ወታደራዊ አምባ እንዲመሰረት በመፍቀዷ የምዕራቡ ዓለም ጥርስ ነክሶባታል። በተጨማሪ፣ የምዕራቡ ዓለም የአፍሪቃ ቀንድን ለመቆጣጠር የሚያደርገውን ጥረት ኤርትራ ለማስቆም ባትችልም፣ እንደ ጎን ውጋት ተደርጋ ትቆጠራለች። የዓብይ መንግስት በወደብ ምክንያት ከኤርትራ ጋር መዋጋቱ እንደማይቀር በሰፊው ማውራት ጀምሯል። እነዚህ ሁሉ ትንኮሳዎችና ማስፈራሪያዎች ለኤርትራ ብሄራዊ ደህንነት ስጋት ስለሆኑ የኢሳይያስ መንግሥት ንቆ የማይተዋቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ የሚገኙ ሀገራትም የጦርነቱ ገፈት ቀማሽ በመሆናቸው በአንድ ወይ በሌላ መልክ ተሳታፊ ይሆናሉ። በአጭሩ፣ ጦርነቱ ቀጠናዊ መልክ ሊይዝ ይችላል። ይህ ብቻ አይደለም፣ የኤርትራ ከአማራውና ከፋኖ ጎን መሰለፍ እጅግ መጠነ ሰፊ ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ እንድምታን ያረገዘ ነው። የምዕራቡ ዓለም፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እጇን እንድታወጣ ውትወታውን ይጀምራል። ሰሚ ጆሮ አያገኝም። ከዚያም፣ በዩክሬን እያደረገ እንዳለው፣ የምዕራቡ ዓለም በፌደራል መንግስቱ የሚመራውን የብሄረተኛ ሀይሎችን ስብስብ በመሳሪያ፣ በገንዘብ፣ በዲፕሎማሲና በመሳሰሉት ሁሉ ይረዳል፣ ይተባበራል።በአንፃሩ፣ የሩስያ መንግስት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከኤርትራ፣ ብሎም ከአማራውና ከፋኖጋ ይወግናል። በመሳሪያ፣ በገንዘብና በሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ለመተባበር ይሞክራል። ሌሎች የ "ብሪክስ" ሀገራትም ጎራ ወደመለየት ሊገፋፉ ይችላሉ። የተባበሩት መንግስታትም ሌላ የዲፕሎማሲ ጦርነት የሚካሄድበት አውድማ ይሆናል። ሁኔታው የእስራኤልን መንግስት ደህንነት የሚመለከት ስለሆነ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ የሚሉ ኃይሎችን ልትወግን ትችላለች።

ከላይ ከተጠቀሱት ኩነቶች በተጨማሪ፣ ፋኖ ከአማራው ክልል ተሻግሮ በሌሎች ክልሎችና አካባቢዎች ካሉ አጋሮች ጋር መስራት ይጀምራል። የውጊያ አድማሱም ይሰፋል። መከላከያው በየአቅጣጫው ይወጠርና ኃይሉ እየተዳከመና እየተከፋፈለ ይሄዳል።

### ሊሆን ከቻለ 5 - (Scenario 5) - ፋኖ ሰፊ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ስራ ያከናውናል

ህወሃትም ሆነ ኦነግ ከፌደራል መንግስቱ ጎን እንዳይሰለፉ፣ ፋኖ ሰፊ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ስራ ያከናውናል ብለን እንገምት። በተጨማሪ፣ በሊሆን ከቻለ 2 (Scenario 2) ላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ገፋፊነት ጭምር ፋኖ በሀገሪቱ ለሚገኙ ኃይሎች ሁሉ ጥሪ በማድረግ አሁን ያለውን መንግስት ያላካተተ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ለማቋቋም የሚረዳ እርሾ እንዲጣል እርዳታ አበረከተ እንበል። ይህ የጊዜያዊ የሽግግር መንግስቱን ለማቋቋም የሚፈጠረው አካል፣ እስከ ጊዜያዊ መንግስቱ ሊያደርስ የሚችል ፍኖተ ካርታ ያዘጋጃል። ከዚያ በኋላ ሂደቶች የራሳቸውን ፈለግ ተከትለው ይዘልቃሉ።

### ሊሆን ከቻለ 6 - (Scenario 6) - ሁለቱም ወገኖች ጥሪውን ይቀበላሉ እንበል።

በውጭ ኃይል አደራዳሪነትም ሆነ በሌላ መንገድ፣ በፌደራል መንግስቱና በፋኖ መሀል የተኩስ ማቆም ሂደት እንዲጀመር ግፊት ይደረጋል። ሁለቱም ወገኖች ጥሪውን ይቀበላሉ እንበል።

ይሁንና ሂደቱን ለመጀመር፣ ፌደራል መንግስቱ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፤ ይጠበቅበታል። እነሱም፣

1/ በነሐሴ ወር 2015 ዓም የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማንሳት - በኢትዮጵያ ህገ መንግስት በአንቀጽ 93/4/ለ መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲታወጅ፣ "የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ሥልጣኑ በህገ መንግስቱ የተቀመጡትን መሰረታዊ የፖለቲካና የዲሞክራሲ መብቶችን፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማወጅ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማስወገድ ተፈላጊ ሆኖ በተገኘው ደረጃ እስከማገድ ሊደርስ ይችላል" ይላል። ስለሆነም፣ የፖለቲካና የዲሞክራሲ መብቶችን የሚገድበው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ካልተነሳ ምንም ዓይነት ውይይት አይቻልም።

2/ ወደ አማራ ክልል የተላከው ግዙፍ የመከላከያ ሃይል ስምሪቱን በይፋ አቁሞ ከአማራ ክልል መውጣት ይኖርበታል፣

3/ የአማራውን ህዝብ የማንነትና በሠላም በሀገሩ የዜግነቱ መብቱ ተከብሮለት የመኖር መብቱን ለማስከበር በአዲስ መልክ ተደራጅቶ እየታገለ ያለው ፋኖ፣ በመንግሥት እየተሰጠው ያለው አጉል ፍረጃ ቆሞ ህጋዊ እውቅና ሊሰጠው ይገባል፣

4/ በአማራው ህዝብና በሌሎች የሀገራችን ዜጎች ላይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ ባለሥልጣኖችን ጥፋታቸው እየተጣራ ለፍርድ የሚቀርቡበትና፣ በሀገራችን ውስጥ ተጠያቂነት እንዲጀመር የሚደረግበት ሁኔታ እንዲኖር መግባባት መፍጠር፤ መንግስት በፍኖተ ሰላም፣ በቡሬና በባህርዳር፣ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ላይ በድሮን የጨፈጨፋቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችና ሌሎች ሰላማዊ ዜጎች ላይ እርምጃ የወሰዱት ባለሥልጣናት ለፍርድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

5/ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝና ያለ አሳማኝ ምክንያት የታፈሱና የታሰሩ ሁሉ መፈታት አለባቸው - በተለይም በአማራነታቸው ብቻ ከየቤታቸውና ከየመንገዱ እየተለቀሙ የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ መፈታት ይኖርባቸዋል፣

6/ መንግስት በይፋ ስለድርድሩ፣ በሠላማዊ መንገድና ተአማኒነት ባለው አካሄድ ለመደራደር ስላለው ዝግጁነትና ስለ ዓላማው ይፋዊ መግለጫ መስጠት አለበት፣

7/ ቢያንስ የአፍሪካ አንድነት በታዛቢነት የሚገኝበትና ሁሉም ተደራዳሪዎች በሚስማሙበት ገለልተኛ ሥፍራ ድርድሩ እንዲካሄድ መንግሥት ዝግጁነትን መግለጽ አለበት።

እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርጎ ወደ ድርድር መግባት ይቻላል። እንዲያ ማድረግ ከተቻለ፣ ኢትዮጵያ ከመሞት ተርፋ ለዜጎቿ ቤዛ ሆና ትቀጥላለች። ልጆቿም እጅግ አስከፊ ከሆነ ችግር፣ እንግልት፣ ውርደትና ሀፍረት ይተርፋሉ። ለኢትዮጵያ የተሻለ ምርጫዋ ቢሆን 6ት ነው። አብዛኛዎቹ ምርጫዎች ለኢትዮጵያ የሞት ግብዣ ናቸው። ኢትዮጵያም ሆነች ዜጎቿ ዓይናቸው እያየ፣ ግን ሳይፈልጉ ተገደው የሚገቡበት ስምጥ ገደል ነው። ያ እንዳይሆን ከተፈለገ፣ የሕዝቡ ምርጫ በስራ እንዲተረጎም ሁሉም የሚቻለውን ማድረግ ይጠበቅበታል።

በአጠቃላይ ቀደም አድርገን በሰነዱ እንደገለፅነው፣ ይህ ሁኔታ ከቀጠለ ኢትዮጵያ የተደቀኑባትን ህልውናዋን የሚፈታተኑ ችግሮችን አሳይተናል። በመጨረሻም ምን ሊሆን እንደሚችል መላምቶችን አስቀምጠናል። ኢትዮጵያን ከአስከፊ ሁኔታ ለማዳን ሁሉን አካታች በሆነ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውልና ታሳቢ እንዲሆን ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ከዚህ የሚከተለውን የአገር አድን ፍኖተ ካርታ አቅርበናል።

## የአገር አድን ፍኖተ ካርታ

## ክፍል 2

**የ63 ዓመታት አገዛዝ ያስከተለው መዘዝ**

- ሰብኢዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመረገጣቸው፣ ህዝቡ መብቱን ተነፍጎ ቆይቷል፣
- ህዝቡ ከከፋ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ሊወጣ አልቻለም፣ የኑሮ ውድነቱም ጣራ ነክቷል፣
- የዘር/የዘውግ ልዩነትን መሰረት ያደረገ ግድያና ፍጅት ተካሂዷል፣ በመካሄድ ላይም ይገኛል፣
- የፖለቲካ ስልጣን ድርጅቶች እጅ የገባው በህዝቡ ሙሉ ፍላጎትና ተሳትፎ ሳይሆን፣ የምርጫ ሂደቶችን በማጭበርበር ነው መንግስቶች ሁሉ ስልጣን ላይ ሊቆናጠጡ የቻሉት፣
- እነዚህ መንግስታትም፣ አካታች አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ውለው አድረው በአንድ አምባገነን ስር ይወድቃሉ፣
- በረሃብ፣ በፖለቲካ ልዩነት፣ በጦርነትና በተመሳሳይ ችግሮች ምክንያት ሚሊዮኖች አልቀዋል፣ ረግፈዋል፣
- ዛሬ በተለያየ የሀገሪቱ ክፍሎች ከስምንት ያለነሱ የታጠቁና የተደራጁ ታጣቂ ኃይሎች ይገኛሉ፣
- ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ደብዛው ጠፍቶ፣ ሀብት ስልጣን በያዙ ቡድኖች ቁጥጥር ስር ይገኛል፣ ሙስናም ጣሪያ ነክቷል፤
- ዛሬ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የህዝብ አመኔታ አጥቷል፣
- ከሁለት ዓመት በፊት፣ መንግስት ወደ 5 ሚሊዮን ከሚጠጋ የትግራይ ክልል ህዝብ ጋር ጦርነት ገጠመ፣ ብዙ ሰው አለቀ፣ ንብረት ወደመ፣
- ዛሬ በአማራ ክልል ከ30-40 ሚሊዮን ህዝብ የሚደገፍ ጦርነት በመካሄድ ላይ ይገኛል፣ ዕልቂቱ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው፤
- በኦሮምያ ክልልም አምስት አመት ያህል የቆየ የትጥቅ ትግል በመካሄድ ላይ ነው፣
- በተለያየ የሀገሪቱ ክፍሎች፣ በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ ግጭቶች እየተበራከቱ በመሄድ ላይ ናቸው፣
- ዛሬ፣ በርካታ አካባቢዎች፣ የአዲስ አበባ አካባቢ ጭምር፣ ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ሆነዋል፣
- መንግስት በከፍተኛ ፍጥነት መግዛት እየተሳነው፣ ህዝቡም እምቢተኝነቱን እያሳየ ይገኛል።

በክፍል 1 እንዳየነው፣ ለ63 ዓመታት ያህል መንግስታት ቢቀያየሩም፣ ኢትዮጵያ ከገባችበት የችግር አረንቋ መውጣትዋ ቀርቶ ሁኔታው ተባብሷል። ዛሬ ያለጥርጥር አስጊ በሆነ ደረጃና መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። አሁን ያለው ሁኔታ መፍትሄ ሳይበጅለት ከቀጠለ ምን ሊከተል እንደሚችል በክፍል 1 ትንተና ላይ ተዘርዝሯል።

በቀጣይ ትኩረት የምናደርገው መፍትሄው ላይ ነው። አንዱና ዋነኛውም፣ አካታች ሥርዓትና ሁሉን አቃፊ መንግስት እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል እናመላክታለን።

**ዓላማና ግብ**

የዚህ ፍኖተ ካርታ ዓላማና ግብ እንዲሁም መዳረሻ፣ ላለፉት 63 ዓመታት ሲነሳ የባጀውንና በርቀት እንደሚታይና ደረስንበት፣ ጨበጥነው ስንል እንደሚሸሸው የተንጣለለ የበረሃ ላይ ውሃ ምስል፣ (mirage) አልያዝ አልጨበጥ ያለው የህዝባዊ ሥርዓት መመስረት ጉዳይ ነው። ይህ ሥርዓት፣ በርግጥም ዴሞክራሲያዊ የሆነ፣ ማለትም ነፃ፣ ፍትሃዊና ርትዓዊ፣ ተዓማኒነት-ያለው እንዲሁም አካታች የሆነ ምርጫ ሂደትና ይዘት ያለው፣ አለት ላይ እንደተመሰረተ ቤት ነፋስና ጎርፍ ተፈታትኖ የማያናጋው፣ ቢያንስ በብዙው የሀገሪቱ ሕዝብ ይሁንታና ድጋፍ ያገኘ፣ ለሀገሪቱ መሰረታዊ የፖለቲካ ችግሮች ቁልፍ ጉዳዮች መፍትሄዎችን የሚያስገኝ፣ ለዘመን ተሻጋሪ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊና ለሌሎች ጥያቄዎች ዘላቂ የሆነ መንገድ የሚዘረጋ፣ አቅጣጫ የሚሰጥና ጉዞም የሚያስጀምር ነው። ይህ አዲስ፣ ዴሞክራሲያዊና አካታች ሥርዓት፣ የኢትዮጵያን ሕብረ-ብሄራዊ ቀለም እንደ በረከት ቆጥሮ፣ ይበልጥ ደማቅና አሸብራቂም አድርጎ፣ አስውቦና ተንከባክቦ በመጠበቅ፣ ለተተኪ ትውልድና ለልጅ ልጅ የሚያስረክብ ነው።

ይህ ሥርዓት፣ ልዩነትን ሳይሆን የሀገሪቱን ልጆች የሚያመሳስሉና አንድ የሚያደርጉ እሴቶችን በማጎልበትና በመገንባት፣ ኢትዮጵያን ላለፉት አምስትና ስድስት አስርተ አመታት ያህል በጥላቻ ከጨቀየችበት ሁኔታ ወጥታ፣ የፍቅር መለምለሚያ፣ ማበቢያና ማፍሪያ እንድትሆን ያደርጋል። በተጨማሪ፣ በዓለም ዙሪያ የተከበረች፣ ሉዐላዊነቷን ያስጠበቀች የነፃነትና የማትደፈር ምኩራብ ትሆናለች። ከተመጽዋችነት ወጥታ፣ ልጆቿን ከመንከባከባ ባሻገር፣ ለተቸገሩ የሌላ ሀገር ህዝቦች እጆቿን የምትዘረጋ ሀገር ለማድረግ ነው።

በታሪክ እንደምናውቀው እንደቀደምት ጊዜ፣ ኢትዮጵያ የባህልና የስልጣኔ ተምሳሌት በመሆን እንደገና ፈር ለማስያዝ እንድትችል ማብቃት ነው። ልጆቿ በሀገራቸው መኖር አቅቷቸው፣ ስደት እንዲመርጡ በሁኔታዎች ተገደዋል። በየበረሃው ወዳድቀው፣ የቀማኞችና የአውሬ ሲሳይ ሆነዋል። በባህር ሰምጠዋል። የግፈኞች የጥይት ማብረጃዎች ሆነዋል። እናም፣ ሀገርን አራቁተውና እነሱም ባክነው ከመቅረት ለማዳንና ኢትዮጵያዊነት የሚያሸማቅቅና የሚያሳፍር ሳይሆን፣ የሚወደድና የሚከበር ገፀ-በረከት ማድረግ ነው።

ይህችን ከላይ የሳልናትን ኢትዮጵያ ለማምጣት የህዝቦቿን ትብብርና ለ63 ዓመታት በየመንገዱ ሲፈስ የባጀውን የወገኖቿን ደም ማድረቅ ይጠይቃል። ሚሊዮኖች ወድቀዋል፣ በግፍ ተገድለዋል። በየቦታው በግፍ ታርደው የተጣሉ ልጆች አጽም ነብስ ይማር ተብሎ በክብር መዘከርና መሸኘት ይኖርበታል። ለ30-40 ዓመታት በመላ ሀገሪቱ የተሰፋፋው የልዩነትና የጥላቻ ፖለቲካ ላይመለስ ተወግዶ ዜጎቿ፣ ልዩነቶቻቸውን እንደበረከትና ፀጋ ቆጥረው አንድነታቸው ላይ በማተኮር ተከባብረውና ተባብረው በግስጋሴ መትመም ይኖርባቸዋል። ኢትዮጵያን ወደዚህ ብሩህ ጎዳና፣ ከተቻለም በእመርታ፣ ለማሻገር ብዙ ማሳብና መልፋት ያስፈልጋል። ይህ ህልም በአንድ ሌሊት አይመጣምና አብዝቶ ማሰብን፣ መምከርን፣ መጨነቅን፣ መትጋትን ማቀድንና መሥራትንም ይጠይቃል።

ልጆቻቸውን የተቀሙ እናቶችና አባቶች እንባቸው አልታበሰም፣ አሁንም "እህህ!" እንዳሉ ናቸው። ትምህርት ቤቶችና ሀኪም ቤቶች ወድመዋል፣ መንገዶች፣ ድልድዮችና በበርካታዎቹ የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ የነበሩት ጥቂት ፋብሪካዎችም ፈራርሰዋል። በአጭሩ፣ ከ50 አመት በላይ በተካሄዱት ጦርነቶች የሀገራዊ ኢኮኖሚም ሆነ የማህበራዊ ዘርፎችና የልማት፣ እንዲሁም ፖለቲካዊና ሀገረ-መንግስታዊ ሥርዓት-ግንባታ ቆሟል። እንዲያውም፣ ለዘመናት የተገነቡት በርካታ ተፈላጊ እሴቶቻችን እየደበዘዙ ሄደው ብዙ ዓመታት ወደ ኋላ ተጎትተዋል፣ አያሌዎቹም ፈርሰዋል፣ ፈራርሰዋል። ረሃብ ሚሊዮኖችን እያጠቃ ነው። የኢኮኖሚ ችግሩም ሚሊዮኖችን አዳርሷል። ከመከላከያው ሌላ በርካታ የታጠቁና የተደራጁ ኃይሎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ።

ቤተክርስትያናትና መስጊዶች ክብራቸውን ተነፍገውና ተንቀው በተወሰኑ ክፍሎች ምልከታም ረክሰዋል። ለውድመትም ተዳርገዋል። ፀሎትና ዱአ በማድረግ ምህረት ልንጠይቅ ይገባል።

**ተራራው ጫፍ ለመድረስ**

ተራራው ጫፍ ደረስን ለማለት የምንችለው የምናልመውን፣ ዓላማና ግብ አድርገን የያዝነውን፣ ህዝባዊ ሥርዓት ለመመስረት ስንችል ነው። ከላይ በመጠኑ እንደዘረዘርነው፣ ተራራው ጫፍ ለመድረስ ግን፣ በ63 ዓመት ጉዟችን መንገዱን ሌሎችም ሆኑ እኛ አበላሽተነዋልና ገና ብዙ መጓዝ፣ ብዙ መኳተን፣ መድከም፣ አቀበት መውጣት፣ ቁልቁለት መውረድ፣ በአጭሩ ሳንታክት በቁርጠኝነት በመገስገስ ከግባችን መድረስ ይኖርብናል። ጊዜ ይፈጃል እንጂ ከቆረጥንና ከጣርን እንችላለን። ያን አድርገን ከተሳካልን፣ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ቢያንስ የተሻለ ዕድል ይገጥመዋል። ሰንደቅ ዓላማውንም በክብር ተረክቦ ለመጪ ትውልድ ያስረክባል።

## የሽግግር መንግስት ለምን ያስፈልጋል?

ቋሚና ዘላቂ ሥርዓት ለመገንባት በተቀዳሚ የሚያሻግር መንግስት መምረጥ/መቋቋም ይኖርበታል፤ ይህም ጊዜያዊ ወይም የሽግግር ጊዜ መንግስት ሊባል ይችላል። ስሙ እንደሚያመላክተው መዳረሻ ሳይሆን ወደታሰበው ዓላማና ግብ ለመድረስ መተላለፊያ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ሥርዓት ነው። ድልድይ ሲገነባ በዘላቂነት እንዲያገለግል፣ ሰፊ ጥናት ይደረግበታል። ድልድዩን የሚሸከመው መሬት አቅም፣ የነፋስና የውሃው ግፊት፣ በቀን ውስጥ በድልድዩ ላይ የሚያልፈው መኪናና ተጓዥ ብዛትና ዓይነት፣ ወዘተ፣ ይጠናል። አሻጋሪ ይሆናል ብለን የምንገምተው የሽግግር መንግስትም ሰፊ ዝግጅትና ጥናትን ይጠይቃል። ድልድይ ዋና ስራው በሰላምና ያለችግር ማሻገር ነው። ከወንዙ፣ ከገደሉ፣ ወዲህና በወዲያ በኩል ስላለው ሁኔታ እምብዛም አይመለከተውም። የሽግግር መንግስት ግን፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙዎቹ ሀገሮች ከከፍተኛ ግጭትና ምስቅልቅል ማህበራዊ ችግሮች ለመውጣት የሚጣጣሩ በመሆናቸው ከባድ ኃላፊነቶችን ይሸከማል። ተቋሙ ሲገነባም ሰፊ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል።

ይህን መሰሉ መንግስት፣ በዘላቂነት ሊገነባ ለታቀደው የፖለቲካ ሥርዓት መደላድሉን ያመቻቻል። የሀገሪቱ ህጋዊ መዋቅሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ፣ ሰብአዊ ሙብትና የፖለቲካ ነፃነት እንዴት ሊጠበቁ እንደሚገባቸው፣ ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ (sustainable) የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት የሚያስችል አሰራርና መንግስታዊ መዋቅሮች ለቀልጣፋ አሰራር ምቹ ሆነው እንዲዘረጉ፣ ገለልተኛና በመርህ ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት እንዲሰፍን አስፈላጊውን ሁሉ ዝግጅት የሚያደርግ ነው።

## የሽግግር መንግስት ዋና ዋና ስራዎች

1. የሽግግር መንግስቱን ስለሚመሰርቱት አባላት መስፈርት ማዘጋጀት፣
   - 1.1. የመጀመሪያና ዋናው ጥያቄ አካታችነቱ፣ ማለትም የተገለለ ወገን ወይንም የተረሳ ድምጽ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ሲሆን፤ ይህን መሰሉ የተረሳ ድምጽ ካለ ውሎ አድሮ ቅሬታው ነፍስ ይዘራና፣ ተከታዩ ችግር ሥርዓቱን ይፈታተናል።
   - 1.2. የሽግግር መንግስቱን ዝርዝር የስራ መመሪያ ማዘጋጀት፣
     - 1.2.1. ጊዜያዊ አሰባሳቢ አካል ማቋቋም፣
     - 1.2.2. የሽግግር ጊዜ መንግስት ወይም ሰፋ ያለ ሚና ያለው የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል መመስረት፣
2. የሽግግር ጊዜ የፍትህ ሥርዓት ማዘጋጀትና ለዘመናት ሲፈጸሙ የነበሩ በደሎችን መመርመርና መፍትሄ መስጠት፣
   - 2.1. በደልና ግፍ የፈጸሙ ሁሉ እውነት ተናግረውና ተናዘው ይቅርታ እንዲጠይቁ ማድረግ፣
   - 2.2. መጸጸታቸውና የበደላቸው መጠን ታይቶ አስፈላጊ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ፣
   - 2.3. በመላ ሀገሪቱ ሁሉም እንደሃይማኖቱ "ሱባዔ" ገብቶ ይቅርታ መለመን፣
   - 2.4. በመላ ሀገሪቱ የብሄራዊ እርቅ ሥነስርዓት መፈጸም፣
   - 2.5. የተበደሉ ዜጎችን መካስ፣
3. ሀገሪቱ እየተመራችበት ያለው ሕገ መንግሥት እስከሚሻሽል ድረስ መስናከል የሚፈጥሩ፣ ሽግግሩን ሊያደናቅፉ የሚችሉ አንቀጾችን ለቅሞ አውጥቶ በጊዜአዊነት እንዲታገዱ ማድረግ፣
4. አዲስ፣ ዴሞክራሲያዊና አካታች የሆነ፣ ዘመኑን የሚዋጅ ሕገ-መንግሥት የሚዘጋጅ ኮሚሽን መመስረት፣
5. ረቂቁን ሕገ-መንግሥት የሚያጸድቅ የሕገ-መንግሥት ምክር-ቤት የሚመረጥበትን ወቅትና ሁኔታ መወሰንና ማመቻቸት፣
6. በህገ መንግስቱ ላይ ተመስርቶ ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ አስፈላጊ ተግባሮችን በዕቅድ ማከናወን፣ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

የሽግግር ጊዜ መንግስት ወይም የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ምስረታ ዕውን ከመሆኑ በፊት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መነሳትና ሌላ ቦታ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርጎ ሁሉም ወገኖች ወደ ድርድር መግባት ይችላሉ።

**የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ምስረታ**

የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉን ለመመስረት፣ በመጀመሪያ፣ ከመንግስት፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከታጠቁ ኃይሎች፣ ከሲቪል ማህበራት፣ ከብዙሃን ድርጅቶች፣ በውጭ ሀገራት ከሚገኙ የኢትዮጵያውያን ድርጅቶችና ከሌሎች የተውጣጣ ጊዜያዊ አሰባሳቢ አካል በፈቃደኛነት ከተሰባሰቡ ሀገር ወዳድ ዜጎች፣ ምሁራን፣ የእምነት ተከታዮችና ሌሎች ይመሰረታል። የጊዜዊው አስባሳቢ አካል ዋነኛ ኃላፊነት የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይልን ማቋቋም ሲሆን፣ ያ አካል እንደተቋቋመ ጊዜያዊ አሰባሳቢ አካል ይከስማል።

**የጊዜያዊ አሰባሳቢ አካሉ ተግባራት**

- የስራ መመሪያውን ያዘጋጃል፣
- ለስራ ማስኬጃ የሚሆን በጀት ከራሱና ከሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እንዲበረከትለት ይጠይቃል፣
- በአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉ አካላት/አባላት የምርጫ መስፈርት ያዘጋጃል፣
- ለአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል የሚመጥንና የሚሆን መታዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ጊዜው ሲደርስም፣ በግብረ ኃይሉ እንዲጸድቅ ያስደርጋል፣
- የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ ዓላማና ግብ ምን እንደሆነ የሚዘረዝር ሰነድ ያዘጋጃል፣
- በመስፈርቱ መሰረት የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ተወካዮች ተመርጠው ቃለ መሃላ ይፈጽማሉ፣ ኃላፊነት ተከፋፍለው ስራ ይጀምራሉ።
- የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ስለመቋቋሙና ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ያሳውቃል። ተቋሙን እንዲተባበሩት ያሳስባል። ከዚያም ይህ አካል ራሱን ያከስማል።
- ግብረ ኃይሉ ከፈለገው ይህ አካል በአማካሪነት ሊቆይ ይችላል።

**ጥቂት ስለአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ**

የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል፣ ከመንግስት፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከታጠቁ ኃይሎች፣ ከሲቪል ማህበራት፣ ከብዙሃን ድርጅቶች፣ ከእምነት ተከታዮች፣ በውጭ ሀገራት ከሚገኙ የኢትዮጵያውያን ድርጅቶችና ከሌሎች በፈቃደኛነት ከተሰባሰቡ ሀገር ወዳድ ዜጎች፣ ምሁራንና ከሌሎች ይመሰረታል።

- የግብረ ኃይሉ የስራ ዘመን ከ6 ወራት የማይበልጥ ይሆንና፤ሦስት ወቅቶች ይኖሩታል፣
- ወቅት 1 - የቅድሚያ ወቅት (የሚወስደው ጊዜ ይወሰናል)
- ወቅት 2 - የመካከለኛ ጊዜ ወቅት (የሚወስደው ጊዜ ይወሰናል)
- ወቅት 3 - የረዥም ጊዜ ወቅት (የሚወስደው ጊዜ ይወሰናል)

**ወቅት 1- የቅድሚያ ወቅት ተግባሮች፣**

- አገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ፣ አገራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራና፣
- የውይይት አጀንዳ ያዘጋጃል፣
- ጊዜያዊ የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
- ግብረ ኃይሉ ሊያከናውናቸው የሚገባቸውን ዝርዝር የስራ መመሪያዎች ይሰጣል፣
- ግብረ ኃይሉን ሊረዱ የሚችሉ ባለሙያዎች ይመለምላል/ይመርጣል፣
- አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ውሳኔዎችንም ያደርጋል።
- ውይይቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድና እንዲገባደድ፣ ለአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ ልዩ ጥበቃ የሚያደርግ ተቋም ይመሰረታል፣ ይህ ተቋም የተለያዩ ዘርፎች የሚኖሩት ሲሆን፣

- ልዩ ጥበቃውን የሚመራ አካል ይፈጠራል፣ ይህ አካልም በራሱ በግብረ ኃይሉ የሚመራ ይሆናል፣ በዚህ አካል መሪነት፣
    - የጥበቃ ስራ የሚያካሂዱ፣
    - የምግብ ዝግጅት ላይ የሚሰማሩ፣
    - ማናቸውም ዓይነት የአገልግሎት ስራ የሚያካሂዱ፣
    - ከመዝናኛ ጋር የተያያዙና ሌሎች ተግባሮችን ያጠቃልላል፣
- ስብሰባ የሚካሄድበት ቦታ አስተማማኝና በማንኛውም አካል፣ የመንግስት ጭምር፣ ሊደፈር የማይችል፣ ለምሳሌ በውጭ አገራት ቁጥጥር ስር ያለ ቦታ ሊሆን ይችላል፣
- ስለ ደህንነት ጉዳይ ቀዳሚ መመሪያ ይዘጋጃል፣
- ውይይቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲገባደድ አስፈላጊ ቅድመ-ዝግጅቶችን ያደርጋል፣
- ህጋዊነቱን እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
- የሚያስተላልፉቸው ውሳኔዎች አሳሪነታቸውን በህግ ያረጋግጣል፣
- በህገ መንግስቱ የተካተቱ ሆኖም ለግብረ ኃይሉ ስራ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ህጎች፣ ለምሳሌ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ በጊዜያዊነት እንዲታገዱ ያስደርጋል፣
- የሚያግዙ ተቋማትን ይመሰርትና የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እንዲተባበሩ ያደርጋል፣
- በጀት እንዲመደብ ወይም ከለጋሽ ሀገሮችና ግለሰቦች እንዲሰበሰብ ያስደርጋል፣
- የውይይቱን ሂደት ለመከታተል ይቻል ዘንድ የሚድያ ፖሊሲ ያዘጋጃል፣
    - በግብረ ኃይሉ የግንኙነት ኃላፊ አማካይነት በየዕለቱ የውይይቱ ውጤት ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፣ ገለፃዎች፣ ማብራሪያዎችና ቃለ ምልልሶች በተመደቡ ግለሰቦች አማካይነት ይሰጣሉ፣
    - የሚድያ አካላት ውይይቱን እንዲከታተሉ ይፈቀዳል፣
    - በየጊዜው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ይሰጣሉ፣
- በየክልሉ የሚካሄዱ ጦርነቶች መቆማቸውንና የሰላም ድባብ በአገሪቱ ሁሉ መስፈኑን ያረጋግጣል፣ በደሎችም በአስቸኳይ እንዲቆሙ ያስደርጋል፣
- የፖሊስና የፀጥታ ኃይሎች ከህዝብ ጋር በመተባበር እንዲሰሩ ያስደርጋል፣ ግብረ ኃይሉ በስራ ላይ በሚቆይበት ጊዜ በደሎች የፈፀሙ የፀጥታ ኃይሎች ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ያስወስዳል፣
- የውይይት አካሉ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ተግባራትን በሚያከናውንበት ጊዜ፣ የመንግስት መዋቅሩ መደበኛ ስራውን ያካሂዳል፣ ለምሳሌ፣
    - የትምህርት፣ የግብር፣ የጉሙሪክ፣ የመገናኛ፣ የጤናና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት የሥራ ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ይደረጋል፣
    - የንግድ ተቋማት የምግብና የሸቀጣቀጦች አቅርቦት ለህዘቡ እንዲቀርቡና እንዳይስተጓጎሉ ያደርጋሉ፣
    - ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችም በአግባቡ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣
    - ተጨማሪ መመሪያዎች ያውጣል፣
    - ከውጪ አገር መንግሥታት ጋር ምንም ዓይነት አዳዲስ ውሎች እንዳይደረጉ ያግዳል፣
    - የመንግሥት ሠራተኞች መሥሪያ ቤቶቻቸውን በቅርብ እንዲከታተሉ መመሪያ እንዲተላለፍ ግብረ ኃይሉ ያስደርጋል፣
    - የገንዘብና የቁሳቁስ እንቅስቃሴዎች ከተለመደው አሰራር ውጪ እንዳይንቀሳቀሱ ግብረ ኃይሉ የሚከታተልበት ብልሃት ይፈጥራል፣
    - የንግድ ተቋማት የምግብና የሸቀጣሸቀጦች አቅርቦት ለህዘቡ እንዲቀርቡና እንዳይስተጓጎሉ መመሪያ አውጥቶ መንግስታዊ ተቋማት እንዲተባበሩ ይጠይቃል፣
    - እና ሌሎች ተዛማጅ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
    - ለአገራዊ የውይይት ጉባኤና ለሥራ ማስኬጃ ገንዘብና ቁሳቁስ ማሰባሰብ በአገርና በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በሂደቱ እንዲሳተፉ ያደርጋል፣

- የሽግግር ጊዜ ህጎችንና ደንቦችን ያወጣል፣ እነሱም፣ ከህገ መንግስቱ ውስጥ ከሰፈሩ ህግጋት የሚለዩ ከሆነ የበላይነት (over-riding power) ይኖራቸዋል፣
    - የሽግግር ጊዜ ህጎቹና ደንቦቹ የሚከተሉት ኃላፊነቶችንና ሌሎችን የሚዳስሱ ይሆናሉ፣
        - የስራ አስፈጻሚውን ስልጣን፣
        - የሽግግር መንግስት ምስረታ አስፈላጊነትና ምክንያቱ ላይ ተወያይቶ በተደነገገው መተዳደሪያ መሰረት ውሳኔ ላይ መድረስ፣
        - የሽግግር መንግስቱን ስለሚመሰርቱት አባላት መስፈርት ማዘጋጀት፣ ከዚያም፣
            - የሽግግር መንግስት ምስረታንና የሚቆይበትን ጊዜ መተለም፣
            - የሀገራዊ ምርጫ ጊዜውን በተመለከተ መመሪያ ማዘጋጀት፣
            - የምርጫ ቦርድ ኃላፊነትን በተመለከተ መመሪያ ማዘጋጀት፣
- የፍትህ ሥርዓቱን ስለማሻሻል፣
    - በህገ መንግስቱ ከተደነገገው ውጭ የታሰሩ ሰዎችን በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይደረጋል፣ ያ ሳይሆን ከቀረ አካሉ ተጠያቂ ይሆናል፣
    - የመከላከያና ሌሎች የወታደራዊ ኃላፊዎች ኃላፊነትንና ተግባርን በተመለከተ መመሪያ ያዘጋጃል፣
    - ህገ መንግስቱን ስለማሻሻል መመሪያ ያወጣል፣
    - ኢመደበኛ ወታደራዊ አካላትን በተመለከተና በሌሎች ጉዳዮች ላይ መመሪያዎች ይዘጋጃሉ።

**ወቅት 2 - የመካከለኛ ጊዜ ተግባሮች**

- ይህ ወቅት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ይወሰናል፣
- በዚህ ዘመን ሕገ መንግሥት ይቀረጻል፣ የመንግሥት ተቋማት ሥራቸውን በግልጽነትና በታማኝነት (በፖለቲካ አባላት ሳይሆን) በቴክኖክራቶች መሪነት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፣
- ሀገራዊ ምርጫ ለማካሄድ፣
- የምርጫ ቦርድን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣
- ምርጫን በተመለከተ ተዛማጅ መመሪያዎች ያሰናዳል፣
- የምርጫ ጊዜውን ይወስናል፣
- ስለምርጫው ሂደት መመሪያ ያዘጋጃል፣
- ስለ መራጮች ምዝገባ የጊዜ ገደብ ይወሰንና ይፋ ይደረጋል፣
- ስለፓርቲ አደረጃጀት፣ በተለይም በማንነትና በሃይማኖት ስለመደራጀት መመሪያ ያዘጋጃል፣
- የምርጫ ቦርድ ደንብ መሥፈርት የሚያሟሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝብ ምርጫ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፣
- የሕዝብ ተወካዮች ለአገራዊና ለሕዘባዊ ውክልና በግልፅነትና በምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት ይወዳደራሉ፣
- የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራዊ ምርጫው በነፃ ስለሚወዳደሩበት ብልሃት፣ አገራዊ ራዕያቸውን ስለማስረዳት፣ የሕዝባዊ መገናኛዎችን ፍትሃዊና በእኩልነት ስለመጠቀም፣ ወዘተ መመሪያ ይዘጋጃል፣
- ስለ መንግስት ሠራተኞች ቅጥር፣
- የመንግሥት ሠራተኞች የሚቀጠሩት በትምህርት፣ በተመክሮ፣ በፈተናና በሥራ ብቃታቸው ብቻ ይሆናል፣
- ለሥራ የሚቀጠሩትም በሥራ ቦታ ክፍትነት ላይ የተመረኮዘ ብቻ ይሆናል። የሥራ መደራረብ (duplication) እንዳይኖርና ገንዘብና የሰው ኃይል እንዳይባክን ጥንቃቄ ይደረጋል፣
- ባለፉት አምስት ዓመታትና ከዚያም በፊት የተቀጠሩት በሥራ ብቃታቸው ሳይሆን በማንነታቸው ብቻ ከሆነ ድጎማ እየተሰጣቸው ከሥራቸው ይሰናበታሉ። ክፍት የሥራ ቦታ ካለ እንደማንኛውም አመልክተው ካለፉ የመቀጠር ዕድል ይሰጣቸዋል፣

- በዚህ መሰረት እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት እራሱን እንዲገመግም፣ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠበቃል፣
- በህዝብ መካከል የሚደረገው ውይይትና ትምህርት ይቀጥላል፣ ለዚህም መንግሥትና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶች፣ ተቋማትና በተለይም የኢትዮጵያውያን ሁሉ ትብብርና ርብርቦሽ አስፈላጊነት ወሳኝ ነው።
- ምሁራን፣ ተመክሮ ያላቸው ግለሰቦች፣ አዛውንቶችና ሌሎችም (ህዝባዊ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ህዝባዊ መገናኛዎች፣ ወዘተ) ህዝቡን በማስተማር፣ በማንቃትና አቅጣጫ በመስጠት እዲሳተፉ ይጋበዛሉ።
- በአንገብጋቢ አገራዊ ጥያቄዎች ዙሪያ (የሀገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ስለክልል/ክፍለሀገሮች አደረጃጀት፣ ስለአገራዊ ቋንቋ፣ ኢትዮጵያን ስለማዳን፣ ወዘተ) ውይይት ያካሄዳል።
- በዚህ መሠረት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የህዝቡን ሐሳብ፣ ፍላጎትና ራዕይ አጥንተው (opinion survey) ውጤቶቻቸውን ለአገራዊ ጉባኤው እንዲያቀርቡና እንዲተነትኑ ይጠየቃሉ፣ መፍትሔም ይጠቁማሉ፣

### ወቅት 3 - የሩቅ ጊዜ ዕቅዶች

#### የሀገራዊ ሸንጎ ምስረታ

ብዙውን ጊዜ ይህ አካል የሚፈጠረው አሮጌ ስርዓት በአዲስ በሚታከበት ወቅት ሲሆን፣ አዲስ የሚወለደው አስተዳደር የሚተዳደርበትንና የሚገዛበትን ህጎች ይነድፋል፣ ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡ ይህ ሸንጎ አካታች ከመሆኑ ባለፈ፣ መላ ሕብረተሰብ በመረጠው ወኪል አማካኝነት በአንድ አዳራሽ ተሰብስቦ የወደፊት ዕጣ ፈንታውን የሚወስንበት አጋጣሚ ነው፡፡ ይህ አካል፣

- ሁሉም የሕብረተሰብ አካላት በምርጫ፣ በመረጣቸው ወይም በሌላ ዘዴ ድምፃቸውን ሊያሰሙላቸው የሚችሉ አባላትን መርጠው ለአባልነት ይልካሉ፣
- ሀገራዊ ሸንጎው፣ አሳታፊ የሆነ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ለምሳሌ፣
    - የሚነሱ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በቀላል የድምጽ አሰጣጥ ይወሰናሉ፣
    - ከበድ ያሉና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች ተለይተው ከወጡ በኋላ በከፍተኛ የድምጽ ቁጥር እንዲወሰኑ ይደረጋል፣
    - ግልጽነትና መተማመን እንዲኖር የሚረዱና ሌሎች ህጎች በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ይካተታሉ፣
- የሀገራዊ ሸንጎው ዋነኛ ኃላፊነት ሀገሪቱ የምትተዳደርበትን ህገ መንግስት ነድፎ ስራ ላይ ማዋል ይሆናል፣
- ሕብረተሰቡ ሰፊ ግንዛቤና ትምህርት እንዲያገኝ፣ ሀገራዊ ሸንጎው ጠቃሚና አስፈላጊ ባላቸው ሀገራዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይቶች፣ ትምህርቶች፣ ክርክሮች፣ ወዘተ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣
    - የህገ መንግስቱ ረቂቅ በሁለት መንገድ ሊዘጋጅ ይችላል፣
        - አስቀድሞ ህብረተሰቡን በማሳተፍ በህገ መንግስቱ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ሃሳቦችን በመሰብሰብ፣ ወይም፣
        - ባለሙያዎች አስማርቶ ረቂቅ ህጉን ማሰናዳት፣
    - ረቂቁ ለሀገራዊ ሸንጎ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ህገ መንግስቱ ይጸድቃል፣
- ሀገራዊ ሸንጎው፣ በስራው ሊረዱት የሚችሉ የተለያየ ሙያና ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች ይኖሩታል፣
- በመጨረሻም፣ ሀገራዊ ሸንጎው የወሰነባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ለህዝበ-ውሳኔ ቀርበው ህዝብ ይወስንባቸዋል፡፡
- ሀገራዊ ሸንጎው ስለ አገር አንድነትና ስለአንዳንድ ጉዳዮች ወሳኝ መመሪያ ያወጣል፣
- የውጪ ግንኙነትን በተመለከተ በሽግግሩ ዘመን በውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በኩል ቋሚ በሆኑ ዲፕሎማቶች (career diplomats) መሪነት ለጎረቤት አገሮች፣ ለአፍሪካ አንድነትና ለሚመለከታቸው ሁሉ በየጊዜው ገለጻ ይደረግላቸዋል፣
- አገራዊ ጉባኤ አዘጋጆችና ጊዜያዊ የተቋማት አስተዳዳሪዎች (technocrats) የሽግግሩ መንግሥት ሲያበቃና ቋሚ መንግሥት ሲመሰረት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያከትማል።
- የፖሊስና የፀጥታ ኃይሎች ከህዝብ ጋር በመተባበር እንዲሰሩ ይደረጋል፣
- ከላይ የተጠቀሱት አንዳንዶቹ ተግባራት፣ በጥቂት ወራት ውስጥ ስለማይፈጸሙ በቀጣይነት እንዲሰራባቸው ይደረጋል።

***መደምደሚያ***

*ኢትዮጵያ አደገኛ በሆነ መስቀለኛ መንገድ ላይ ናት። እንደ ሀገር የመቀጠል ወይም የመጥፋቷ ዕጣ ፈንታ በታሪክ አጋጣሚነት ዛሬ በጎልማሳነት ዕድሜ ላይ በምንገኘው በእኛ ትውልድ ላይና በታላላቆቻችንም ላይ ወድቋል። የቅርብ ጊዜ የዓለም ታሪክን ስናይ፣ የዩጎዝላቪያ፣ የሶርያ፣ የየመን፣ የሊቢያ ሁኔታ ሊገጥመን ይችላል። ይህ ደግሞ ከታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶችና ከደም ነጋዴዎች ሌላ ማንኛችንም አናተርፍም። ሀገርና ሕዝብን ለማዳን ጊዜውና ወቅቱ አሁን ነው። ስለዚህም መልሳችን ምን ይሁን? ይህችን አገር ከጥፋት ለማዳን የሁሉንም ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ርብርብ እንደሚጠይቅ ልናስገነዝብ እንሻለን።*

*መፍትሄ አፈላላጊ አገራዊ ግብረ ኃይሉ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች የኢትዮጵያን መፃኢ ዕድል የሚወስኑ በመሆናቸው፣ ዐበይት ውሳኔዎቹ በሕዝበ-ውሳኔ ይቋጫሉ። ይህ ሕዝበ-ውሳኔም በየትኛውም አካል የማይሻር ይሆናል። ይህን የተቀደሰ ዓላማ ለማሳካት ያገባናል የሚሉ ዜጎች ሁሉ ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል።*

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**

## ኢትዮጵያን የማዳን መድረክ / Save Ethiopia Forum

**SaveEthiopiaForum@gmail.com**